# የሰፊው ሕዝብ ድምፅ

ለሰፊው ሕዝብ
(ወዛደር፣ ገበሬ፣ ነጋዴ፣ ወታደር፣ ምሁር፣)
መብትና ጥቅም
የሚታገል ጋዜጣ

ቁጥር 69

ግንቦት 20/1971


## እንደገና ለኢትዮጵያ ተራማጆች የአንድነት ጥሪ

የኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝቦች ባለፉት አምስት ዓመታት ያካሄዱትን ትግሎች ታሪክ ወደፊት በሚመረመርበት ወቅት በአጠቃላይ ሁለት ታላላቅ ምዕራፎች ይኖራሉ:: የመጀመሪያው ምዕራፍ ከየካቲት 1966 እስከ የካቲት 1969 ዓ.ም. ያለው የትግል ዘመን ነው:: ይህ የሶስት ዓመት የትግል ዘመን ምንም እንኳን በዙ ውጣውረድ መነሳት፣ ማጥቃትና መከላከል የተፈራረቀበት ዘመን ቢሆን ቅሉ በአጠቃላይ የኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝቦች በቀንደኛ ጠላቶቻቸው ላይ የአጥቂነት በታን ይዘው ፍጹም ሕዝባዊትና ፍጹም ዲሞክራሲያዊት ወደሆነችው ኢትዮጵያ የሚገሰግሱበት ወቅት ነበር:: ሁለተኛው የታሪክ ምዕራፍ ደግሞ ከየካቲት 1969 ዓ.ም. አንስቶ እስከ አሁንም የምንገኝበት የኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝቦች ትግል ቀስበቀስ ከአጥቂነቱ ደረጃ እየተፈናቀለ አብዮታችን አሁን የሚገኝበት የጣረሞት ደረጃ ላይ የደረሰበት አስከፊ ወቅት ሆኖ እናገኘዋለን::

የመጀመሪያውን የታሪክ ምዕራፍ በሚመለከተው በኩል የኢትዮጵያ ተራማጆች በሙሉ እጅ ለእጅ ተያይዘው በሚሊዮን የሚቆጠሩትን ጭቁኖች በግንባር ቀደምትነት እያንቀሳቀሱ የተቀዳጁትን ድሎች እዚህ ላይ አንመለስባቸውም:: ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብና መላው ዓለም ያውቋቸዋል:: በሁለተኛው ምዕራፍም ቢሆን አድሃሪ ኃይሎች በተለይ ንዑስ ከበርቴውን ደርግ ከተራማጆች ለመነጠል የመነሰሱት ሴራ ከተካሄደ በኋላ ደርግ ከብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም ተንሸራቶ የወደቀበትን አሳፋሪ አዘቅት፣ ይህንን መንሸራተት አሻፈረኝ በሉ ኢትዮጵያዊያን ላይ ያደረሰውን አሰቃቂ ግፍ ዛሬ ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብና መላው ዓለም ያውቁታል:: ስለመንሸራተቱ ጉዳይ አገባብ በሚያዝያ ወር 1968 ዓ.ም. የታወጀውን "የኢትዮጵያ ብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም" አንቀጽ በአንቀጽ እየተመለከተ ዛሬ ከሚያየውና ከሚሰማው ጋር ያነፃጽር እንላለን:: በተራማጅ ኃይሎች ላይ ስለወረደው አመጽ ባለፈው ቁጥራችን እንዳየነው ዛሬ በኢትዮጵያ 20 ሺህ ተራማጅ፣ ዲሞክራትና አገር ወዳድ ኢትዮጵያዊያን "ነፃ አብዮታዊው ደርግ" እሥር ቤቶች በመማቀቅ ላይ እንዳሉ፣ ይህ ቁጥር በኢትዮጵያችን ታሪክ ምንጊዜም ቢሆን ተደርሶበት የማያውቅ በመሆኑ፣ ይህንን ያህል አብዮታዊያን በእሥር ቤት ሲማቀቁ በአፍሪካ ምንም ዓይነት ተወዳዳሪ የሌለው ሁኔታ መሆኑንና በዓለምም የናለበት ቺሊና አርጀንቲና እንጂ ሌላ ተወዳዳሪ ሊኖር እንደማይችል... ባለፈው ቁጥራችን ያቀረብነውን ገምጋማ አገባብ ቃለስ በሉ እንዲመለከት እንጋብዛለን::

ዛሬ በኢትዮጵያ ምድር ከየካቲት 1969 ዓ.ም. ወዲህ በተመነሰሰው አዲስ የቀኝ ኃይሎች ህብረት ምክንያት አብዮታችን ከተሳካይነትም ደረጃ ወርዶ በጣረሞት ላይ የሚገኝበት ሁኔታ አለ:: እዚህ ሁኔታ ላይ እንዴት ደረስን? የሚለውን ጥያቄ ዛሬ በዚህች ጽሁፍ ለመተንተን አንሻም:: የዛች ጽሁፍ ዋና ዓላማ ዛሬ የምንገኝበት ሁኔታ ምንድን ነው? ከዚህስ ሁኔታ ለመውጣት የኢትዮጵያ ተራማጆች ምን ማድረግ አለባቸው? የሚለውን ጥያቄ ለማንሳትና በሌሎች ድርጅቶች ውስጥ ላሉም ሆነ ላልተደራጁ የኢትዮጵያ ማርክሲስት ሌኒኒስቶች፣ ለዲሞክራቶችና ለአገር ወዳዶች ሁሉ መልስ ሊሆኑ ይችላሉ የምንላቸውን ነጥቦች ለውይይት ለማቅረብ ነው::

የዛሬው ሁኔታ ምንድን ነው? የመላ ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ ከተመነሰሰበት ወቅት አንስቶ ዕጣው ከኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝቦች ዕጣ ተለይቶ አያውቅም:: ስለሆነም አዲሱ የቀኝ ኃይሎች ህብረት በኢትዮጵያ ገበሬዎች፣ ወዛአደሮች፣ ወልጋሎቶች፣ ዲሞክራቶች፣ ወጣቶች፣ ምሁራን፣ ሴቶች፣ አገር ወዳድ የጦርና የፖሊስ መኮንኖች ላይ ሲዘምት የዚህን የፀረ ሕዝቦች ጥቃት እስም አብሮ ቀምሶታል:: ሰፍር ቁጥር የሌላቸው አባላት ተረሽነዋል:: በሺህ የሚቆጠሩ አባላት ደጋፊዎች ታሥረዋል:: ተሰደዋል:: ተንገላተዋል:: ነገር ግን ይህ በድርጅት ላይ የተፈጠረው ከፍተኛ ፀረ ሕዝብ አመጽ፣ ለዚህ ፀረ ሕዝብ አመጽ ጥቃት አድርባዮች ያባዩት ተባባሪነት ጭፍን ያለ ጥንቱ ወይም በንዑስ ከበርቴ አልህ ላይ የተመረከዘ አምባገነን አላገፈፋውም:: የስንት ኢትዮጵያዊያን ደም የተገበረበት፣ የስንት ጓደኞቻችን ህይወት የተማገደበት፣ የስንት ጭቁኖች የላብ ተስፋ የተንጠለጠለበት፣ የእናት አገራችን ክብር ተስፋ የተጣለበት የአብዮት ጉዳይ ከማንኛውም ስሜትና ግለሰብነት በላይ ጥሞና



መታየትና መተንተን ያለበት ጉዳይ ነው ብሎ ያምናል:: መኢሶን ዛሬ እንደገና ለተራማጆች ጥሪ ሲያደርግ የሚነሳበት መነሻ ይኸ ነው::

ከዚህ ተነስቶ ዛሬ የኢትዮጵያን ሁኔታ ተረድቶ የወደፊቱን የትግል ጉዳና ለመቀየስ ለሚፈልግ ታጋይ ሁሉ እጅግ ገልጽ የሆኑ አንዳንድ መሠረታዊ ነገሮች አሉ:: ዛሬ የአገራችን ሁኔታ መለክ ከሚሰጡት ነገሮች አንዱ በፖለቲካው መስክ ያለው ከፍተኛ ጥራት ነው እንላለን:: ይህ ያለው የፖለቲካ ጥራት ለአብዮትና ለእናት አገር በለው ለተነሱ ኢትዮጵያዊያን ሁሉ ለትግል ያመቸ ሁኔታ ይፈጥራል:: ታዲያ ወደፊት ለምን አንራመድም? ድልን ለመቀዳጀት ምን ይጎድለናል? የሚለው ጥያቄ ከዚህ ከተትሉ ይነሳል:: መልሱም አጭር ነው:: የቀኝ ኃይሎች ህብረት በአብዮቱ ላይ ባደረሰው ጥቃት የተነሳ የኢትዮጵያ ሕዝብ የትግል መሣሪያ የነበሩት ድርጅቶች ፈራርሰውበታል፣ ግንባር ቀደም የነበሩ እንቅስቃሴዎች በፀረ ሕዝብ አመጽና በአድርባዮች ሴራ ተኮላሽተውበታል፣ አንዳንዶቹም ተበታትነውበታል:: ወደፊት ለመራመድ የግንባር ቀደም ድርጅቶች ጥንካሬ ሲያስፈልግ ፀረ ሕዝቦች እነሱን ለማፈራረስ ሌትተቀን ይፍጨረጨራሉ:: ወደፊት ለመራመድ የግንባር ቀደም ኃይሎች ሕብረትና አንድነት ሲያስፈልግ ፀረ ሕዝቦች ተራማጆችን ለመለያየት ብቻ ሳይሆን በእነሱ ተጠቅመው ሌላውን ለመምታት ይፈጽማሉ:: ይህ ፀረ ሕዝብ ሴራቸው ደግሞ ለነሱ ጥሩ ውጤት አስገኝቶላቸዋል:: በዚህ የተነሳ ዛሬ በሃገሪቱ ላለው የፖለቲካ ጥራትና በሚሊዮን የሚቆጠሩ ጭቁኖች ለሚያሳዩት የትግል ስሜትና ፍላጎት ተመጣጣኝ የሆነ የተራማጅ ድርጅቶች ጥንካሬና ህብረት የለም:: ከዚህ ተነስቶ በዛሬው ሁኔታ አንፃር የተራማጆች ትግል መያዝ ያለበት አቅጣጫ ምን እንደሆነ ለመገንዘብ በዙም አያዳግትም::

ዛሬ የኢትዮጵያ ተራማጆች አንገብጋቢ ተግባሮች አንደኛ ይህ የተገኘው የፖለቲካ ጥራት እንዳይደፈርስ አቅማቸው በሚፈቅድላቸው አጋጣሚ ሁሉ መታገል፣ ሁለተኛ ለአብዮት፣ ለእናት አገር ሊንቀሳቀስ የሚችለውን ይኸ ነው የማይባል ኃይል በግንባር ቀደምትነት ለማንቀሳቀስ የሚያስችላቸውን የህቡዕ መዋቅር መዘርጋት፣ ሶስተኛ ደግሞ ተራማጅ ኃይሎች በሙሉ ከማንኛውም የንዑስ ከበርቴ አልህና ዉቅለኝነት ተወግደው አንድነታቸውን ማጠናከርና በህብረት መታገል አለባቸው እንላለን::

የዚህ ጥሪያችን ዋና ይዘት እንግዲህ በሁለት ይከፈላል:: በመጀመሪያው ክፍል የዛሬውን ሁኔታ ጥንድ መለኮች ለማሳየት እንሞክራለን:: በሁለተኛው ክፍል ደግሞ ከዚህ ሁኔታ የሚፈልቁትን ተግባሮች በተለይ ደግሞ የተራማጅ ኃይሎችን ህብረት በሚመለከት በኩል አንዳንድ ሃሳቦችን ለኢትዮጵያ ተራማጆች እንሰነዝራለን::

### ክፍል 1. የዛሬው ሁኔታ መለኮች

ከላይ እንዳልነው ዛሬ በኢትዮጵያ ምድር የፖለቲካ ጥራት ችግር የለም:: ይህን ስንል ምን ማለታችን ነው? ይህ ማለት በታሪካችን ከመቸውም ጊዜ ይበልጥ ዛሬ የኢትዮጵያ ሕዝብ የትግሉን ዓላማ እጅግ ጥራት ባለው ሁኔታ ያውቀዋል:: ወደዚህ ዓላማ የሚያደርሰውንም የትግል ፋና እንደዚሁ አጣርቶ ያውቀዋል:: ከበዙ ዘመናት ትግል በኋላ ይፋ የወጣው የኢትዮጵያ ተራማጆች የትግል መድረክ ማለትም የኢትዮጵያ ብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም፣ በሙሉ ዘሬያ ለሁለት ዓመታት ያህል የተካሄደው ከፍተኛ ቅስቀሳ፣ ከሥራ ላይ እንዲውል ስፍር ቁጥር የሌላቸው ኢትዮጵያዊያንና ኢትዮጵያዊያት ያፈሰሱት ደም የዚህ የፖለቲካ ጥራት መሠረት ሆኖ እናገኘዋለን:: ይህ ፕሮግራም ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከጥንት እስከ ዛሬ የተንገበገበበት፣ መላው የኢትዮጵያ ወደቡና ሕዝባዊ ሠራዊት ያለቢጣን የገባለት ፕሮግራም ነው:: ይህ ፕሮግራም በዚህ መልክ በግንባር ተቀባይነት የተነሳ እስከአሁን ድረስ በይፋ ሽሬዋለሁ ያለ ኃይል አልተነሳም:: እነሲሳይም ሆኑ እነዓለማየሁ ፕሮግራሙን ሸረው አብዮቱን ለመቀልበስ ሲሞክሩ እንኳ "የኢትዮጵያ ብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ዘገነል" በለው ለመናገር አልደፈሩም:: ግን ሌላም አለ:: ይህ ፕሮግራም በሕዝቡ ፊት በግንባር ተቀባይነት የተነሳ በይፋ ሊሸሩት የማይችሉት ቀልበሾችና ተንሸራታቾች ይህ ፕሮግራም በሰው ጥራት የተነሳ ራሳቸውን ሳያጋልጡ በተዘዋዋሪም ቢሆን ሊሸሩት አይችሉም:: በፕሮግራሙ ጥራት የተነሳ በድብቅ ፕሮግራሙን እየተቃወሙ በአፍ በፕሮግራሙ መድረክ ላይ ነን ለማለት ፈጽሞ አዳጋች ጉዳይ ነው:: ራቅ ሳይሄዱ መጋለጥና በሰፊው ሕዝብ መተፋትን ያስከትላል:: ፕሮግራሙ "ዲሞክራሲ ባስቸኳይ" እያለ "ታንክህ ውሰዱ" ማለት፣ ፕሮግራሙ "ፊውዳል አትፍሚ" እያለ የመጀመሪያ ደረጃ የበዝባዦች እኩልነትን በተምክህተኛ ዐበሪት መርገጥ፣ ፕሮግራሙ "ቢሮክራሲ ይውደም" እያለ ከዚህ ከመነጨ ቢሮክራሲ ጋር ገጥሞ የአብዮቱን በፈር ማጥቃት፣ ፕሮግራሙ "የብሄራዊ ነፃነትና የገለልተኛ የውጭ ፖለቲካ" እያለ የአገሪቱን የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ፣ የባህል፣ የወታደር ተጽእኖ እንደገና ለአዲስ ጌቶች አስረክቦ የእናት አገራችንን ክብር እንዳልነበረ ማውደም፣ ፕሮግራሙ "ሕዝባዊ ድርጅቶች ያብቡ" እያለ ያሉትን ማጠፋትና በፀረ ሕዝብ ሴራ ማፈራረስ፣ ፕሮግራሙ "የወዛአደር ፓርቲ፣ ሌሎችም ዲሞክራሲያዊ ፓርቲዎች" እያለ የወዛአደሩን ፓርቲ ጥንስሶች ማፈራረስ፣ ሌሎች ኢትዮጵያዊያን ተራማጆች እንዳይደራጁ እፍና መያዝ... እነዚህ ድርጊቶችና እነዚህ ሁሉ ዛሬ የቀኝ ኃይሎች ህብረት ሙሉ በሙሉ ከፕሮግራሙ መንሸራተቱን የሚያሳዩ የሚያጋልጡ

# ክንፃ ጋዜጦች

ቁጥር ፪ / 1971

<u>የሰፊው ሕዝብ ድምጽ</u>

— ቁጥር 69 ግንቦት 20/1971 ዓ ም

እንደገና ለኢትዮጵያ ተራማጆች የአንድነት ጥሪ

<u>የአብዮት ፋና</u>

— ቁጥር 20 ሚያዝያ 1/1971 ዓም

ኢማሌድሕ በህብረት ድምፁ ለታሪክ ፍርድ ራሱን ሲያቀርብ

— ቁጥር 21 ሚያዝያ 17/1971 ዓ ም

ሀቀኛ ተራማጆች ተሰብሰቡ

<u>በአኢተማ መጽሔት አዘጋጅ ቦርድ የተቀነባበረ፡፡</u>

ናቸው:: በዚህም የተነሳ ዛሬ የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚፈልገውን ያውቃል፣ ማን የሕዝቡን ፍላጎት እንደሚያረር ያውቃል፣ ማን ከሕዝቡ ጎን እንደተሰለፈ ያውቃል::

ይህንን ጥራት ደግሞ በሰፊና በአደናጋሪ ፕሮፓጋንዳ ማደፍረስ ዘበት ነው:: ለምን? ምክንያቱም አንደኛ የዛሬ ተንሸራታቾች ራሳቸው ዛሬ የከፋትን ቃላቸውን በየአደባባዩ፣ በየሴሚናሩ በያሉበት ገራ እጃቸው ከተከሸቸው ተነቅለው እስኪሄዱ ድረስ ከሕዝቡ ጋር ያስተጋቡ ቸው የነበረ ስለነበረ ዛሬ ቃል ማጠፋቸው የአተላነታቸውን አዘቅት ያባብሰ እንጂ ሌላ የሚያባየው ነገር የለም:: ሁለተኛ ደግሞ ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ በሰፊና በድርጊት መካከል፣ በሃቅና ወሬና በአስመሳይ መካከል ለመለየት የሚያስችለውን በቂ የፖለቲካ ንቃት ከአምስት ዓመት የአብዮታዊ ትግሉ ገብይቷል:: ከሁሉ ይበልጥ የሚያሁና የሚደንቁ በገዱ ከሁሉ ይበልጥ የሕዝብ ወገኖች የሚመሰሉበት ዘመን እስከሚል "የተራማጅ ተራማጅ" መስሎ የተደባለቀውን የኢሕአፓ ፀረ ሕዝብ ወንጋ ከመሃሉ እየፈለፈለ ያወጣውና ወደ ተራ ነፍሰገዳይነት እንዲቀረፅ ያደረገው በዚህ በንቃት ነው:: የቀደሞውን የነዓለማየሁ ኃይሉን የቀኝ ኃይሎች ህብረት ተለካሽ የፖለቲካ መሥመር ፊት ለፊት ገጥሞ አሻፈረኝ ያለው በዚህ በንቃት ነው:: ዛሬ ደግሞ ያው የነዓለማየሁ የፖለቲካ መሥመር በአዲሱ የቀኝ ኃይሎች ህብረት አማካኝነት ሲከሰት አሻፈረኝ ብሎ "ከብሄራዊ ዴሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም ጋር ወደፊት" ብሎ ከፀረ ሕዝቦች ጋር እጅግ አስቸጋሪ የሆነ የትንንቅ ወቅት ውስጥ የገባው ከትግሉ ከዕለት ዕለት እየተማረ፣ ~~አስመሳዮን ከሃቀኞቹ፣ ለፈፋውን ከድርጊት፣ ለመለየት~~ የሚያስችለው የፖለቲካ ጥራት በማግኘቱ ነው::

ፀረ ሕዝቦችም ይህን በታጋይ ኢትዮጵያዊያን ደም የተገኘ ጥራት በአፈጻደቅ ፕሮፓጋንዳ ለማደፍረስ፣ እነሱ ከሃዲዎች ታጋዮች፣ ታጋይ የሕዝብ ልጆችን ከሃዲዎች አድርገው ለማቅረብ ያደረጉት ሙከራ በሕዝቡ ከፍተኛ የትግል ልምድና የንቃት ደረጃ የተነሳ ሙሉ በሙሉ መክሸፉን አላጡትም:: ድርጊትንም ቢሆን የቸገረው ሰዓት ከንፋስ ይጠጋል ነው እንጂ ፀረ ሕዝብ እንጂ ይዞ፣ ዴሞክራሲ አያስፈልግህም፣ የእናት አገርህ ብሄራዊ ክብር ገደል ይግባ፣ የመነበው ቢሮክራሲ ተመሰ ይፈንጭብህ... እያሉ ወደነቃ ሕዝብ ለመጠጋትና ለዚህ ፖለቲካ የሱን ድጋፍ ለማግኘት መሞከር እንደም ተስፋ የሌለው ሞኝነት እሰያም ወደር የሌለው የሕዝብ ንቀት እንደ ሆነ ፀረ ሕዝቦች የተገነዘቡ አይመስለም:: የሆነ ሆኖ ያለውን ጥራት በሰፊፈ ማደፍረስ አልተቻለም:: ስለሆነም ፀረ ሕዝቦች ልክ እንደኢሕአፓው ዘመን፣ ልክ እንደቀደሞው የቀኝ ኃይሎች ህብረት ዘመን፣ በአብዮት ኃይሎች ላይ ተሰማሩ:: ይህ በኢትዮጵያ ተራማጆች ሰፈር የተቃጣው ፀረ ሕዝብ አመጽ በትግሉ ላይ ያስከተለውን ጉዳት ዘቅ ብለን እንመጠብታለን:: እዚህ ላይ ግን ለማለት የምንፈልገው አንዲት ነገር ብቻ ነው:: ይህ አመጽ ምንም ጥፍን ቢሆን፣ ምንም አስከፊ ቢሆን በአብዮቱ ሰፈር ያለውን የፖለቲካ ጥራት እስከዚህም አላደፈረሰው:: አዲሱን የቀኝ ኃይሎች ህብረትም ይበሱን አጋለጠው፣ ይበሱን ፀረ ሕዝብነቱን፣ ይበሱን መክሰሩን አበየበት እንጂ በሕዝቡ ዘንድ ተቀባይነትን አላስገኘለትም:: በዚህም ሁሉ የተነሳ ዛሬ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሌላ ከፍተኛ የሆነ ድል ተቀዳጅቷል:: የኢትዮጵያን አብዮትና የብሄራዊ ክብሯን የወደፊት እድል ከደርግ ለይቶ፣ ከደርግ ባሻገር መመልከት ጀምሯል:: ከመጀመሪያው አንስቶ የመላ ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ ወደሕዝባዊት ኢትዮጵያ የሚደረገው ትግል ገና ከበርቱን ደርግ አንድ የተወሰነ ደረጃ ላይ ጥሎ የሚያልፍ ትግል ነው ሲል ያስተጋባው የነበረው አቋም ዛሬ በሚሊዮን በሚቆጠሩ ኢትዮጵያዊያን አዕምሮ ውስጥ የታነፀ ሃቅ ሆኗል::

ይህ ዛሬ በሃገራችን የሚታየው የፖለቲካ ጥራት እንዲገኝ የመላ ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ እጅግ የሚኮራበት፣ ስፍር ቁጥር በሌላቸው አባላቱ ደም የከፈለው አስተዋጽኦ አድርጓል:: በዚሁ ሃቅ ላይ ትንሽ መለስ ማለት ያስፈልጋል::

እንደሚታወሰው የካቲት አብዮት ከፈነዳ ከአንድ ዓመት በኋላ በጊዜው በነበሩት ተራማጅ ይባሉ በነበሩት ኃይሎች መካከል የሁለት መሥመር ትግል ሲጀመር ተራማጅን ወገን በመወከል መኢሶን በግንባር ቀደምነት ሲሰለፍ የቀለበሹን መሥመር በመወከል ደግሞ የኋላው ነፍሰ ገዳይ ቡድን ኢሕአፓ ነበር:: በዚህ ትግል የአድሃሪዎች ግንባር ቀደም የነበረው ኢሕአፓ ድል ከተመታ በኋላ የፖለቲካ ክስረቱን ለመሸፈን ሲል በነፍሰ ገዳይነት ተሰማርቶ እጅግ በዙ የመኢሶን አባላትንና ደጋፊዎችን ስፍር ቁጥር የሌላቸው ሌሎች አብዮታዊያንን እያደነ ገደለ:: የመሥመር ትግሉ ኢሕአፓ ቢተፋ አላቆም:: ከዚህ ጋር በተያያዘ ሁኔታ የቀደሞው የነዓለማየሁ ኃይሌ የቀኝ ኃይሎች ህብረት በአንድ በኩል፣ በጊዜው የነበሩት የደርግ ተራማጆች መኢሶንና ሌሎች ተራማጅ ድርጅቶች በሌላ በኩል መካከል እንደገና ሌላ ትግል ተጀመረ:: በዚህም ትግል በግንባር ቀደምነት የተሰለፈው ንቅናቄያችን አሁንም እንደቀደሞው ውድ ጓደኞችን እየሰዋ በሃቀኛው መሥመር ስር መታገሉን ቀጠለ:: የነዓለማየሁ ኃይሌ የቀኝ ኃይሎች ህብረት እናት ላይ ተመቶ ከተፈረከረከ በኋላ አብዮቱ ትንሽ ሳምንታት ወደፊት መገስገስ እንደ ጀመረ የነዓለማየሁ ኃይሌን ቀለበሽ የፖለቲካ መሥመር ይዞ ሌላ አዲስ የቀኝ ኃይሎች ህብረት ተነሳ:: የአንዳንድ የቀደሞ ተራማጆችና የአድርባይ ድርጅቶች ሠፈር መለወጥና በቀደሞው በነዓለማየሁ ፖለቲካ ሥር መሰለፍ በሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ፊት ውዥንብርን ፈጥሮና እስካሁን የተገኘውን የፖለቲካ ጥራት ሊያደፈርስ የሚችል ሁኔታ ፈጠረ:: እርግጥ ውሎ አድሮ ይህንን መንሸራተት ለመገንዘብ የሚያስችለው ንቃት ነበረው:: ነገር ግን በዚህ ወቅት አዲሱን ዙር የመሥመር ትግል በሕዝብ በኩል፣ በአብዮት በኩል ፍንቶ ለመምራት የሚችል ግንባር



ቀደም ኃይል እጅግ አስፈላጊ ነበር:: ስለሆነም መኢሶን ይህንን የግንባር ቀደምነት ኃላፊነት ያለአንዳች ማመንታት ተቀበለ፣ ከተንሸራታቾች ጋር መንሸራተቱን አሻፈረኝ ብሎ በአብዮቱ ሰፈር በመጽናት እነዓለማየሁ ከተመቱ በኋላ በተከተሉት ወራት ከፍተኛ የሁለት መሥመር ትግል ካሄደባቸዋል:: በዚህ ትግል ውስጥ ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከዳር እስከዳር የነዓለማየሁን ቀለበሽ ፖለቲካ በተቃወመበት ወኔና ቆራጥነት የአዲሱን የቀኝ ኃይሎች ሕብረት መሥመር ተቃወመ:: ሚያዝያ 23 ቀን 1969 ዓ.ም. የወዝአደር ቀንን ምክንያት በማድረግ ባካየው ሰልፍ ይህ የሰፊው ሕዝብ አቋም፣ ይህ ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ በመኢሶን ግንባር ቀደምነት ለተወረለው አብዮታዊ መሥመር ለመቆየቅ ዝግጁ መሆን ለወዳጅም ለጠላትም ይፋ ሆኖ ታየ:: በዚህም የተነሳ በሰፊው ሕዝብ ሰፈር ያለውን የፖለቲካ ጥራት ለመቋቋም አዲሱ የቀኝ ኃይሎች ህብረ የኪሣራው ምልክት በሆነው ፀረ ሕዝብ አመጽ ተሠማራ::

እንግዲህ በዚህ ወቅት አንስቶ ለመኢሶንና ለጠቅላላው የኢትዮጵያ አብዮታዊያን ያለው ምርጫ ግልጽ ነበር:: ወይ አሁንም ደርግ የያዘው መሥመር ትክክል ነው፣ አድርባይ ድርጅቶች የሚያስተጋቡት ፖለቲካ አብዮታዊ ነው፣ ብሎ በመቀላመድ ከተንሸራታቾች ጋር "እበሮ መብላት"፣ ከፀረ ሕዝቦች ጋር ተሻርኮ በአብዮቱ ጣረሞት ላይ ከሚደረገው "የስልጣን ድልድል" ድርሻውን ተቀብሎ የኢትዮጵያን ሕዝብ መክዳት፣ በታጋይ ጓዶች ንፁህ ደም ተገንቶ የነበረውን የፖለቲካ ጥራት ገደል መወርወር፣ ወይ ደግሞ የተያዘውን ለአብዮታችንም ሆነ ለብሄራዊ ነፃነታችን እጅግ አደገኛ የሆነውን የፖለቲካ መሥመር መታገሉንና ማጋለጡን ቀጥሎ ለማንኛውም መስዋዕትነት ራስን ማዘጋጀት:: መኢሶን የትግል ስልት ለውጥ ከማድረጉ በፊት የነበሩት ሁለት ሦስት ወራት ለኢትዮጵያ ተራማጆች በሙሉ ዓይኑን አፍጦ ቀርቦ የነበረው ምርጫ ይኸ ነበር:: መኢሶን በታሪክ ፊት የተቀበለውን አደራ በማክበር የወሰደው ምርጫ ሁለተኛውን የትግል፣ የክብርና የመስዋዕትነት ጉዳና ነበር:: በነሐሴ ወር 1969 ዓ.ም. ይህንኑ ትግል በተሻለ ሁኔታ ለመቀጠል የትግል ስልት ለውጥ ያደረገውም ከዚህ ታሪካዊ ምርጫ ተነስቶ ነበር::

ይህ እርምጃ ለመኢሶን ብቻ ባይሆን ለጠቅላላው ለኢትዮጵያ ተራማጆች ታላቅ የፖለቲካ ድል ነው:: ይህንን የምንልበት በዙ ምክንያቶች አሉን:: መኢሶን በዚያን ጊዜ ለቀረበለት ወሳኝ ምርጫ ፊት በፀረ አብዮትና በአብዮት ጉዳና መካከል እያመነታ ቢቀጥል ኖሮ፣ "የደርግ ታሪካዊ ሚና እያከተመ ሲሄድ አብዮታዊያን ከሱ ጋር የሚያደርጉት ትብብር ያከትማል" ብሎ የገባውን ቃል ባያከብር ኖሮ፣ በደርግና በአድርባዮች በአንድ በኩል በመኢሶንና በሌሎች አብዮታዊያን በሌላ በኩል ያሉት ልዩነቶች እንደዚህ ግልጥልጥ ባለ ሁኔታ ተፈረጥርጠው ባይወጡ ኖሮ፣ ቢጥሩ የአብዮቱን ሰፈር መፈክሮችና ስፍር ቁጥር የሌላቸው ሰማዕታት የተከፈለ ቸውን ዓላማዎች አንስቶ መኢሶን ከቀኝ ኃይሎች ህብረት ራሱን ነጥሎ ወደፊት ለመጓዝ አስቦ ሳገኘውን እርምጃ ባይወስድ ኖሮ ዛሬ አብዮታችን ይገኝበት የነበረውን የፖለቲካ ውዥንብር ማን ሊገምተው ይችላል? መኢሶን አዲሱን የቀኝ ኃይሎች ህብረት በሰፊው ሕዝብ ፊት፣ ከሰፊው ሕዝብ ጋር ሆኖ መዋጋትን ትቶ እንደተቀረት አድርባይ ድርጅቶች ወሪያች በፖለቲካ መሥመር ጥያቄ ላይ ሳይሆን በቦታ ክፍፍል በይገባኛል አይገባህም ውስጥ ውስጡን ሲራኮት ቢመታ ኖሮ ለኢትዮጵያ ተራማጆች ምን ያህል አሳፋሪ የሆነ የትግል ምዕራፍ በተጻፈ ነበር? በዚህ ሁኔታ መሠረታዊ የሆኑትን የሕዝብ ጥያቄዎች በአድርባይነት ሸጦ ከአዲሱ ፀረ ሕዝብ ኃይል ጋር በጥቅም በተሳሰረ ኖሮ፣ ከሁለት ዓመት ወዲህ በአብዮቱ ስም የተደረጉትን ፀረ ሕዝብና ፀረ ኢትዮጵያ ክብር ድርጊቶች በአብዮትና በብሄራዊ ነፃነት ስም በግንባር ቀደምነት የሚቋቋም ኃይል ባይኖር ኖሮ "የተሰውትን ጓዶች አርማ አንስተን እንቀጥላለን" ያልነበትን ቃል ኪዳን ምንኛ በከዳን ነበር?

ይህ እንዳይሆን መኢሶን እርምጃው የሚያስከትለውን መስዋዕትነትና ችግር አውቆ፣ ፈቅዶና መዝኖ በመቀበል የአብዮታችንና የኢትዮጵያ እናታችን ክብር የሚጠይቀውን እርምጃ ወሰደ:: በአብዮቱ አንገብጋቢ ጥያቄዎች ሁሉ ደርግ በአብዮቱ ስም ከሚያመለክተው የቀለበሰ ጉዳና ሌላ አማራጭ፣ ሌላ የሃቀኛ አብዮት ፋና እንዳለ መኢሶን ማንኛውንም መስዋዕትነት እየተቀበለ ማስተጋባቱንና ማሳየቱን ቀጠለ:: ደርግና አድርባይ ድርጅቶች አብዮቱንና የእናት አገራችንን ነፃነት ይዘው ወደመቀመቅ በማምራት ላይ መሆናቸውን፣ የአብዮትና የእናት አገር ክብር ጉዳና መኢሶን የሚያመለክተው መሆኑን ሕዝቡ የተቀበለው ሃቅ ከመሆኑም ሌላ ዛሬ በነዚህ ሁለት መሥመሮች መካከል ይካሄድ የነበረውን ትግል ዋና ዋና መልክ ስንመለከት መኢሶን ያመለከተው መሥመር ምንኛ ትክክለኛ እንደነበር በማያሻማ ሁኔታ ለመረዳት ይቻላል::

አዲሱ የቀኝ ኃይሎች ህብረት በአብዮቱ ስም የሰፊውን ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ መብቶች ሲረግጥ መኢሶን "ዴሞክራሲያዊ መብቶች ለጭቁኖች አሁኑኑ" ብሎ ከሰፊው ሕዝብ ጋር የትግል አርማውን አነሳ:: የኢትዮጵያ አብዮት በደረሰበት ደረጃ የሰፊው ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ መብቶች ባስቸኳይ ካልታወቁ ከእንግዲህ ወደኋላ እንጂ ወደፊት እርምጃ እንደማይገኝ አስታወቀ:: በሃገሪቱ የተፈጠሩት የሰፊው ሕዝብ የእራሱ ሕዝባዊ ስልጣን ጥንስስ የሆኑት ሕዝባዊ ድርጅቶችና የሰለሰሰው ቢሮክራሲ እንደዚያ በተፋጠጠበት ሁኔታ ትግሉ እንዴት እንዴት ሲያጠፋ ስለማይበርድ ሕዝባዊው ስልጣን ፀረ ሕዝቡን ቢሮክራሲ እንዲደመስስ ዴሞክራሲ ያስፈልገዋል ሲል መኢሶን በቆራጥነት ታገለ:: ይኸ ካልሆነ ሕዝባዊ ድርጅቶች ተዳክመው እንደሚጠወልጉ የአድሃሪው ቢሮክራሲ አሽከር አገልጋይ እንደሚሆኑ መኢሶን ተናገረ:: ዴሞክራሲያዊ መብቶች መታፈናቸውን ቀጠሉ:: በዚያው ልክ ደግሞ አድሃሪው ቢሮክራሲ አይሉ ዛሬ ከነአሠሚ አገነቱ ቀጠ

ሊያቸው፣ የገበሬ ማህበራትና ሌሎች ሕዝባዊ ድርጅቶች "ሕዝባዊነታቸው" የወደመበት ደረጃ ደረሱ::

ቢሮክራሲ ከሌለ "የተራማጆች ህብረት" የሚባለው ቅጥፈት መሆኑን፣ ያለቢሮክራሲ ሃቀኛ ሕብረት ለመመሥረት አለመቻሉን መኢሶን ተናገረ:: እኒሁ የቀኝ ኃይሎች ሕብረት ቢሮክራሲን ማፈን ቀጠለ:: ለቁነቶቹን በቢሮክራሲያዊ ወደይት መፍታት ያልቻለው "ኢማሌድህ" ዝቅ በለን እንደምናየው ከፍተኛ ኪሣራ ላይ ወድቆ ተንኮ ከተንገዳገደ በኋላ ዛሬ ዉርስ መፍረሱ በይፋ ተነገረለት!

ቢሮክራሲ ከሌለ የብሄረሰቦች ችግር እየተባባሰ ይሄዳል እንጂ ለኢትዮጵያ አንድነት መፍትሄ የሚሆን ምንም ነገር ደርግ ከያዘው ትምክህተኛ ፖለቲካ ሊወጣ አይችልም ያለው መኢሶን ለብሄረሰቦች የተሟላ እኩልነትና ለኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝቦች አንድነት የሚደረገውን ትግል መለያየት እንደሌለበት አስገነዘበ:: በጦር ኃይልና በትምክህተኝነት መሠረት ላይ የተገነባው የደርግ ፖለቲካ የኢትዮጵያን ሕዝቦች አንድነት አናግቶ በዚህ በኩል የኋሊት አንድ ወደፊት አንጓሰራመደን ዛሬ ከመቼውም ጊዜ ይበልጥ ግልጽ ነው::

እኒሁ የቀኝ ኃይሎች ህብረት የውጭን ጠላት ለመቋቋም ከአድሃሪ ኃይሎች ጋር እንታረቅ፣ ሁሉም ነገር ወደጦሩ ግንባር እያለ የቀለበሰ ፖለቲካውን ሲደረድር በመኢሶን ግንባር ቀደምነት የሚንቀሳቀሱ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ጥያቄዎች "ዐርቅ አንፈልግም ተዋቅ!" "ቢሮክራሲው አያዘምትም ይዘመትበት" "አብዮታዊት እናት አገር ወይም ሞት" በለው ተሰለፉ:: የቀኝ ኃይሎች ህብረት የያዘው ጉዳና ምናልባት የሃገሪቱን ድንበሮች ለማስከበር ቢችልም በምንም ዓይነት የኢትዮጵያን አብዮት ከቀለበሳ የሚያድን ጉዳና አልነበረም:: ይከ ፖለቲካ በጦርነት ግርግር ፀረ ሕዝብ ኃይሎችን ቁልፍ ቦታ የሚያስይዝና የሚያጠናክር ፖለቲካ ነበር:: መኢሶን ያራመደው የፖለቲካ መሥመር ግን የሃገሪቱንም ሀልዉና፣ አብዮታችንንም የሚያድን ፖለቲካ ነበር:: እኒሁ የቀኝ ኃይሎች ሕብረት የተከተለው መሥመር የሰጠው ውጤት መኢሶን "የተነበየው" ውጤት ነበር:: "አያዘምትም ይዘመትበት" በተባለው በአድሃሪው ቢሮክራሲ አማካኝነት በሚካሄድ ጦርነት ሊሳው የርቀት ድንበርን እንኳን ለመከላከል አልተቻለም:: አድሃሪው ቢሮክራሲ በግርግር በያዘው ቦታ በመጠቀም በሚሊቴሪው ውስጥም ሆነ በሚሊሺያው ውስጥ ግንባር ቀደም ተራማጆችን እየለቀመ መምታት፣ በመቅሰል ሳው በጦርነቱ ጥረት ላይ ይከ ነው የማይባል አሻጥር እየፈጸመ የሃገሪቱን ችግሮች ማባባስና ሁኔታውን ለቀለበሳ ማመቻቸትን ተቶ በጦሩ ግንባር ዱላን ይፈልጋል ማለት ዘበት ነበር! በመሆኑም ደርግ የአድሃሪውን የሚሊቴሪ ቢሮክራሲ አሻጥር ለመገንዘብ በዙም ጊዜ አልወሰደበት:: ግን ታዲያ ይህንን ተገንዝቦ ወደሕዝቡ ወደሃቀኛው መሥመር ተመለሰ? የለም:: ይህንን ከማድረግ ፈንታ፣ ለጦርነቱ አስፈላጊ የሆነውን አብዮታዊ አመራር ከማስገኘት ፈንታ፣ "አብዮታዊት እናት አገር ወይም ሞት" እያሉ ለእናት አገራቸውና ለአብዮታቸው ለመሞት የተዘጋጁ በሺህና በመቶ ሺህ የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን እያሉ ደርግ በአድሃሪው ቢሮክራሲ አሻጥር የተነሳ በየግንባሩ ለተፈጠረው ችግር ያገኘው መፍትሄ የውጭ ጦር ወደ ሃገሪቱ አስገብቶ ማዋጋትና የሃገራችንን ክብር ማስደፈር ነበር! አድሃሪው ቢሮክራሲ ሲያዘምት አልቻለም:: ግን ደግሞ የሱን አሻጥር ተደጋጋሚ በከፍተኛ መስዋዕትነት ዱላን በተቀዳጀው መደበኛውና ሕዝባዊ ሠራዊት ላይ፣ የፈለገ ቀራጭነት ቦታ ይዞ የጠቀመው ይኸው አድሃሪው ቢሮክራሲ እንደሆነ ግልጽ ነው:: መኢሶን ቀደም ሲል ደርግ የተከተለው "የብሄራዊ ዐርቅ" ፖለቲካ ዞር ዞር አብዮት የሚያስቀለብስ አደገኛ ፖለቲካ ነው ያለው ለዚህ ነበር:: ይህ ደግሞ ዛሬ ለማንም ግልጽ ሆኖ የሚታይ ሃቅ ነው::

እኒሁ የቀኝ ኃይሎች ህብረት የተከተለው በውጭ ኃይሎች ላይ የመተማመን ፖለቲካ አንደኛ ይህንን ሕብረት አጠናክሮ በፀረ ቢሮክራቲክ ገጽታው እንዲገፋበት፣ "ከነፃ፣ ከተደራጀና ከታጠቀ ሕዝብ ትግል" ፊር የጀመረውን ማፈግፈግ እንዲቀጥል፣ ሰፊው ሕዝብ ጥያቄዎቹ ጀርባ ሰጠ ማለት የጀመረውን ፊሊፕ ሥራ ቁ ብሎ እንዲይዘው የሚያግዝ፣ ሁለተኛ ደግሞ አገራችንን በኃያላን መንግሥታት በተራ ቴክኒያዊ ገበጣ ጨዋታ ወደ ተራ ጠጠርነት የሚያዋርድ፣ ብሄራዊ ነፃነታችንን አስደፍር በዓለም ሕዝቦች ፊትና በተለይ በአፍሪካ ሕዝቦች ፊት እንደገና "የአህጉር ሃፍረት" የሚያደርገን ሁኔታ የሚያመጣ አደገኛ ፖለቲካ መሆኑን መኢሶን ተናገረ:: በጡ ፈንታ የአብዮቱን ችግሮች ለመወጣት እርግጥ የውጭ እርዳታ ያስፈልጋል ግን ከሁሉ በላይ የሕዝቡ መንቃት፣ መደራጀትና መታጠቅ ላይ መተማመን እንደሚያስፈልግ፣ እርዳታው ከዚህ የአብዮት ጉዳና የሚያርቅ እርዳታ እንዳይሆን፣ በእርዳታ ሰበብ ብሄራዊ ነፃነታችንም እንዳይደፈር፣ እርዳታ በአጋዥነት እንጂ በወሳኝነት ደረጃ መቀመጥ የለበትም ሲል ተከራከረ:: የደርግ ፖለቲካ በሁለቱም በኩል ዛሬ የት ላይ እንደጣለን ግልጽ ነው::

በዚህ ዓይነት በዙ መቀጠል ይቻላል:: ጥሩሩ ለማስቀመጥ ግን ዛሬ የኢትዮጵያ አብዮትና የሃገሪቱ ብሄራዊ ነፃነት የሚገኙበትን መቅመቅ የተመለከተ ሰው መኢሶን ያራምደው የነበረውና አሁንም የሚያራምደው መሥመር ምን ያህል ትክክለኛ እንደነበር በቀላሉ ሊረዳው ይችላል:: ይህንን የምናነሳው ከዛሬ ሁለት ዓመት ጀምረን ባነሳናቸው ከደርግና ከአድርባይ ድርጅቶች መሪዎች ጋር በነበረን ፉክክሮች የእኛ እምነት ትክክል ነበር ብለን "ታሪክን" ለመጻፍ አይደለም:: መኢሶን አንስቶት የነበረት ጥያቄዎች አሁንም የአብዮቱ አንገብጋቢ ጥያቄዎች ናቸው:: አሁንም ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚጠይቃቸው ናቸው:: ዛሬ ከመቼውም ጊዜ ይበልጥ የነዚህን ጥያቄዎች ትክክለኛነት፣ ሕዝቡ በመኢሶን ቅስቀሳ ብቻ ሳይሆን በተጨባጭ በሚሰማውና በሚያየው ተረድቷል:: ስለሆነም ዛሬ ሰፊው ሕዝብ የሚፈልገውን ያውቃል:: ማን በአብዮቱ ሠፈር እንዳለ፣ ማን ከአብዮቱ ተገንጥሎ ወደ ታሪክ አተላነት በመንጉድ ላይ እን



ደሆነ ያውቃል::

ይህ የፖለቲካ ጥራት ደግሞ በቀላሉ የሚደፈርስ አይደለም:: እንዲያውም በመጭው ጊዜ በዚህ በኩል ይበልጥ ጥራት እየተገኘ ይሄዳል:: ለምን? ምክኒያቱ አጭር ነው:: እኒሁ የቀኝ ኃይሎች ሕብረት በመደብ ይዘቱ የተነሳ የኢትዮጵያን አብዮትና የሃገሪቱን ብሄራዊ ነፃነት ለሚመለከቱት ጥያቄዎች ለአንደኛቸውም ተገቢውን መልስ ለመስጠት ከዕለት ዕለት ይበልጥ እየተሳነው እንደሚሄድ ከአሁኑ "ለመተንበይ" ይቻላል:: በዚህም የተነሳ ይህ ከዕለት ዕለት በአድሃሪው ቢሮክራሲና በውጭ ኃይሎች ቁጥጥር ስር እየገባ የሚሄደው "ህብረት" በጠቅላላው በብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም ላይ ፀንተው ከቆሙ ኃይሎች ጋር በሙሉ ከዕለት ዕለት የባሰውን እየተቃረረ፣ የባሰ ቀራኔ ውስጥ እየገባ ይሄዳል:: በዚህም የተነሳ ከገባበት አዙሪት ውስጥ ለመውጣት የሚቀረው መንገድ የባሰውን ከቢሮክራሲውና ከውጭ ኃይሎች ቁጥጥር ስር መውደቅ እንደሆነ ግልጽ ነው:: ባለፈት ወራት ከመኢሶን አባላት ሌላ በተጨማሪ ከወዝሊግ፣ ከሌፕሊግ፣ ከሰደድ ከራሱ አንዱ ክፍል ጋር እየተፋጠ የሄደው ቀራኔ የኢትዮጵያን አብዮት አንገብጋቢ ጥያቄዎችን ለመመለስ ያልቻለው የቀኝ ኃይሎች ሕብረት ይበልጥ በአድሃሪው ቢሮክራሲ ቁጥጥር ሥር እየወደቀና በሃገሪቱ ባሉ ተራማጅ ኃይሎች ጋር እየተባባሰ የሚሄድ ቀራኔ ውስጥ እየወደቀ መሄዱን የሚያሳይ ሂደት ነው::

በሌላ በኩል ደግሞ መጭው ጊዜ በብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም ላይ ለተሰለፉ ኃይሎች ለትግላቸው ይበልጥ ምቹ እንደሚሆን የዚያኑ ያህል ግልጽ ነው:: መጭው ጊዜ ለጸረ ቢሮክራሲ፣ ለብሄረሰቦች እኩልነት፣ ለኢትዮጵያ ብሄራዊ ክብርና ነፃነት፣ ለሃቀኛ የተራማጆች ህብረት... ለሚታገሉ ኃይሎች እንጂ ለፀረ ቢሮክራሲ፣ ትምክህተኝነት፣ ለብሄራዊ ውርደት ለቆሙ ጥቂቶች እንዳይደለ ባይታለም የተፈታ ጉዳይ ነው:: ስለሆነም የኢትዮጵያ ተራማጆች በመበቀትና ባለተገረመበት የገዐሰ ከበርቴው መደብ መንሸራተት በምንም ዓይነት ሳይሸበሩ፣ በአቋማቸው ትክክለኛነት ብቻ ሳይሆን በዚሁ ትክክለኛነት ዘላቂነት ሙሉ በሙሉ በመተማመን ጊዜ ለእነሱ እንጂ ለተንሸራታቾች እንዳልሆነ ለማወቅ፣ የታሪክ ሂደት ለእነሱ እንጂ በቀለበሾች በኩል እንዳልሆነ በመረዳት ለመጭው የትግል ምዕራፍ በጥሞናና በዲሲፕሊን፣ በቆራጥነትና በመጭው ዱላ በማይጠራጠር መንፈስ ራሳቸውን ማዘጋጀት አለባቸው:: ይበሳን ለታሪክ አተላዎች አንድ ቢሮክራሲያዊት ኢትዮጵያ እንደሆነች፣ ሕዝባዊት ኢትዮጵያ እንደሆነች፣ የተፈራች ነፃ ኢትዮጵያ እንደሆነች፣ ከአብራኳ ከምታወጣቸው ታጋይ ልጆቿ ትግልና ደም በፊውዳሊዝም፣ በኢምፔሪያሊዝምና በቢሮክራሲያዊ ካፒታሊዝም መቃብር ላይ ትገነባለች::

ይህንን በሳለን መጭው ጊዜ አስቸጋሪ የትግል ጊዜ አይሆንም ለማለት አይደለም:: የፖለቲካ ጥራት በቻውን ፀረ ሕዝቦችን ተደምሮ ዱላ አያደርግም:: ግን ይከ ራሱ በኢትዮጵያ ግንባር ቀደም ኃይሎች እጅ ያለ ከፍተኛ የትግል መሣሪያ ነው:: በነሐሴ 1969 ዓ.ም. የትግል በለተ ለውጥ ባደረገበት ሰዓት በዚህ ጉዳይ ላይ እንደሚከተለው ብለን ነበር:: "የኢትዮጵያ ሕዝቦች ለነፃነትና ለእኩልነት፣ ለሰላምና ለወደፊት እርምጃ የሚያደርጉት ትግ ዱሉ እንደዛሬ አመቼ ሁኔታን አገኝቶም አያውቅም:: ችግሮቻችንና ድክመቶቻችን፣ የአብዮታችን መበከርና የሃገራችን መወረር ጊዜያዊ ናቸው:: ዘላቂነት የላቸውም:: የፖለቲካ መሥመር ትክክለኛነት ወሳኝ መሆኑን በመገንዘብ፣ ፖለቲካን አስቀድመን ችግርንና ሞትን ሳንፈራ በሰፊው ሕዝብ ተማምነን እስከመጨረሻው ለመታገል ቆርጠን ከተነሳን፣ አንድነታችንን አጠንክረን ወደፊት ከተራመድን የፈጀውን ጊዜ ቢፈጅም የፈለገውን መስዋዕትነት ቢጠይቅም ድልን እናሸንፋለን"::

ይህ እንነጋገር ሙሉ በሙሉ ትክክል ነበር:: ግን አንዱን አብዮት ለማራመድ ምን ያህል ትክክለኛ እምነት ቢይዙ አቅምም ያስፈልጋል:: ዛሬ ባለው የሃገራችን ተጨባጭ ሁኔታ እንዲያውም አንገብጋቢ የሆነው ጥያቄ እስከዚህም ለሰፊው ሕዝብ የትግል አቅጣጫዎችንና ዓላማዎችን መጠቆም ሳይሆን በሕዝቡ ዘንድ ተቀባይነት ያገኘውን መሥመር ከሥራ ላይ ለማዋል የሚያስፈልገውን ኃይል መሰብሰብና ማደራጀት ነው ብለን እንገምታለን:: የቀኝ ኃይሎችም ይሄንን ያውቁታል:: የትግል መሣሪያ የሆኑትን ድርጅቶችንም በሙሉ ያፈራረሱት፣ ግንባር ቀደም አባሎችንና አደራጆችን በሙሉ የረሸኑትና በየእሥር ቤት ያጎሩበት፣ ተራማጅ የፖለቲካ ድርጅቶችን ለማፈን የመከረበት ዋናው ምክኒያትና ከዚያም "ተገለህ ውበድ" በለው ያሸፈተ ለዚህ ነው:: የቀኝ ኃይሎች ይህንን የፖለቲካ ጥራት ማደፍረስ ስላቃታቸው፣ ይህ መሥመር ከሥራ ላይ እንዳይውል በዚሁ ቁልፍ በሆነው የመደራጀት ጥያቄ ላይ ተረባርበዋል:: ተራማጆች ደግሞ በፖለቲካው መሥመር ጉዳይ ባገኙት ይህ ነው የማይባል ዱላ ላይ ተመሥርተው በዚሁ ቁልፍ ጥያቄ ላይ መረባረብ አለባቸው:: የጊዜው አንገብጋቢ ጥያቄ ይከ ነው::

አወን! ዛሬ የሃገራችንን ሁኔታ ሌላ መልክ የሚሰጠው ባለው እጅግ አመቺ በሆነና <u>ከዕለት ዕለት ለአብዮታዊያን ይበልጥ አመቺ እየሆነ</u> በሚሄደው የፖለቲካ ጥራት አንፃር ቢታይ ይህንን ፖለቲካ ከሥራ ላይ ሊያውለው የሚችለው ኃይል ሁኔታው በሚጠይቀው ልክ አለመደራጀቱና ኃይሉን አለማስተባበሩ ነው:: በዚህም የተነሳ የጊዜው ዋና አንገብጋቢ ጥያቄ የግንባር ቀደም ድርጅቶች ኃይላቸውን ማጠናከርና ተራማጆች በቀኝ ኃይሎች ሕብረት ቢራና ተገኩሎ የተበታተነውን ህብረታቸውን እንደገና መገንባት ነው እንላለን:: ይህንን ተግባር ዉዘቸ ቁራቹን ሁለተኛ ክፍል እስክንመለስበት ድረስ ዛሬ በድርጅት ጉዳይ ያለንበትን የመዳከምና የመበታተን ሁኔታ መመልከት ይጠቅማል::

እንደማንኛውም መስከ በቀኝ ሃይሎች ህብረት ቢሮ የተነሣ በዚህ በድርጅትም መስከ የተገኙት ዶሎች ሁሉ ተበትነዋል፡፡ የኋሊት ጉዞ ተደርጋል፡፡ ይህ በድርጅት ጎዳና ላይ አገራችን ያደረገችው የኋሊት ጉዞ ከብዙ አንፃር ሊታይ ይችላል፡፡ በመጀመሪያ በአብዮት በፊት ተደራጅቶ ይገኝ ከነበረው ሃይል ዛሬ ወይ በአመራር የፖለቲካ ከሥረት የተነሳ ተስፋ እየቆረጠም ሆነ በቀኞች እየተመታ በመበታተን ላይ ይገኛል፤ ወይ ደግሞ በጠራና ግልጽ በሆነ አብዮታዊ መሥመር ተሰልፎ በከፍተኛ ፀረ ህዝብ አመፅ የተነሳ ድርጅቶች ተባከሙዋል፡፡ ከዚህም ከአመራሮች የፖለቲካ ከሥረት ከተከተለው መበታተንና በፀረ'ህዝብ አመፅ ከተከተለው ድርጅታዊ መፃከም ጋር ተያይዞ ዛሬ የኢትዮጵያ ተራማጆች በየካቲት ወር 1969 ዓ.ም ደርሰውበት የነበረው የህብረት ደረጃም ተቀልብሶ እናገኘዋለን፡፡ በዚህ የተነሳ ዝቅ ብለን እንደምናየው "ኢማሌድህ" ይባል የነበረው የህብረት መዋቅር ጠርቦ ከመደምሰሱ በፊት የቀ ላይ "ማርክሲስት ሌኒንስት" የቸኛው ላይ "የድርጅቶች ህብረት" ሊባል እንደሚችል የማይታወቅበት ጥንድ የሆነ የከሥረት ደረጃ ላይ ወድቆ እንደነበር እናያለን፡፡

የተለያዩ በአብዮቱ በፊት የነበረትንም ሆነ ያሉትን ድርጅቶች ሁኔታ እንመልከት፡፡ እዚህ ላይ በአንድ በኩል የ"ግራ" አድርባዮችና የቀኝ አድርባዩ ድርጅቶች ሁኔታ አለ፡፡ የነዚህ ድርጅቶች አመራሮች ተራ በተራ የተከተሏቸው የከሰረ የፖለቲካ መስመሮች ነበሩ፡፡ በዚህም የተነሳ ውሎ ይደር እንጂ ሁሉም ከፖለቲካ ክስረታቸው ጋር የተያያዘ ድርጅታዊ ከስረትና መበታተን መፍረክረክ ደርሶባቸዋል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ዛሬም ቢሆን በሚሊዮን የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን እንገበው የሚታገሉለትን የፖለቲካ መሥመር በገንቦር ቀደምነት እንስቶ የሚዋጋው መኢሶን አለ፡፡ መኢሶን የተከተለውና አሁንም የሚከተለው ፖለቲካ የህዝብ መሥመር ነው፡፡ የፖለቲካ ኪሣራ የለበትም፡፡ ስለሆነም በፀረ ህዝብ ሃይሎች የተሰነዘረበት አመፅ ድርጅታዊ መፃከምን እንጂ ኪሣራን ሊያመጣበት አይችልም፡፡ አላመጣበትምም፡፡ ፖለቲካውና መስመሩ ትክክለኛ ስለሆነ፤ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ማርክሲስቶች፤ ዲሞክራቶችና አገር ወዳዶችም እንደሱ ዲሞክራሲ፤ ብሄራዊ ነፃነት፤ የብሄረሰቦች እኩልነት፤ ሃቀኛ የተራማጆች ህብረት...ስለሚሉ ለጊዜው ሁኔታ መዋቅሩን አስተካክሎ ወደፊት ይጓዛል እንጂ ምንም አይነት አመፅ ሊደመስሰው አይችልም፡፡

በመጀመሪያ ከፖለቲካ ኪሣራ ጋር ድርጅታዊ ኪሣራ የደረሰባቸውን እንመልከት፡፡ ብዙ ጊዜ ተደጋግሞ እንደተወሳው የኢህአፓ ቸብደኞች ትግል በኢትዮጵያ ተራማጆች በተለይም በወጣቱ አካባቢ ያስከተለው እጅግ አስከፊ የሆነ ውጤት አለ፡፡ ኢህአፓ የኢትዮጵያን አብዮት የበደለው በብዙ መቶ የሚቆጠሩ ተራማጅ ኢትዮጵያውያንን መጨረሱ፤ በሃቅና በጥሞና የሚካሄድ ትምህርታዊ ውይይት እንዳይካሄድ አፍኖ እንዱ ታጋይ ትውልድን አደንቁር በቀልበሸ



ፖለቲካው ለማበለፍ መፍጨርጨሩ ብቻ አይደለም፡፡ ዛሬ እንደምናየው መሰሪዎቹ የተከተሉት ሃቀኛ ተራማጅ ኢትዮጵያውያን፤ በከንቱ ከጠፍጭፈው ያለቁትም፤ የኢህአፓ ከሥረት በምንም አይነት በማያወላውል ሁኔታ ይፋ ሲወጣ የወደቀበት ውዥንብርና ተስፋ መቁረጥ፤ ምን ሃቀኛ መሥመር ቢኖር ከሱ ሥር ለመሰለፍ የሚያበቁት ከፍተኛ ጥርጣሬና ማመንታት በጠቅላላው ለፖለቲካ ትግል የሚያበቁት ገለልተኝነት... የኢህአፓ መሪዎች በኢትዮጵያ ታጋይ ትውልድ ላይ የፈፀሙት ታሪክ ቃን ጊዜም ይቅር የማይላቸው ወንጀል እንደሆነ ለማየት አያስቸግርም፡፡

የኢህአፓ ቀልበሸ የፖለቲካ መሥመርና ጀብደኛ የትግል ዘዴ ካስከተለው መበታተን ሌላ ከአንድ አመት ወዲህ ደግሞ የቀኝ አድርባዩ ድርጅቶች አመራሮች የተከተሉት ፖለቲካ ያመጣው ውዥንብርና ድርጅታዊ ከሥረት አለ፡፡ የቀኝ አድርባዩ ድርጅቶች መሪዎች የከሠሩና የኢትዮጵያን ጭቁኖች እንገብጋቢ ጥያቄዎች የሚፃረር የፖለቲካ መሥመር ተከትሉ፡፡ ይህንን መሥመራቸውን የተቃወሙትን ሃቀኛ አብዮታውያንን ከአድሃሪው ቢሮክራሲ ጋር አብረው አባረሩ፡፡ አየጠፈሙ አስያዙ፤ አስገረፉ፤ አስረሸኑ፡፡ ፀረ ህዝብ ፖለቲካቸውን በውጫዊ መልክ "ህዝቡ አባለፈው፤ ህዝቡ ይደግፈናል" እያሉ በሬዲዮና በጋዜጣ አስለፈፉ፡፡ ነገር ግን በዚህ ፖለቲካቸው ኪሣራ የተነሣ ህዝብ እንደራቃቸው፤ ህዝብ ከተፋቸው በኋላ ደግሞ በአሽዋ ላይ የገነቡት "ድርጅታዊ ቤታቸው" ፀረ ህዝቡ ቢሮክራሲ "እፍ" ሲለው እንደሚፈርስ አልተገነዘቡም ነበር፡፡ ነገር ግን ተጠቅመባቸው ከጠረገ በኋላ አድሃሪው ቢሮክራሲ እንደደረቀ ሎሚ ጣላቸው፡፡ አምና ይከተሉት የነበረው ዲሞክራትና አገር ወዳድ፤ አድርባዩ መሪዎች በምን ላይ ከፀረ ህዝቡ ቢሮክራሲ እንደተለዩ ባይገባው እየተደነ ይመታ ጀመር፡ መኢሶን በጭሬህዝቦች በመታ "ዲሞክራሲ" ብሎ ነው፡፡ መኢሶን የትምክህተኞች አመፅ በወረደበት "የብሄረሰቦች እኩልነት" ብሎ ነው፡፡ ...ባጭሩ ፀረ ህዝቦችና ፀረ ኢትዮጵያ ሃይሎች ቢያጠቁት በግልፅና በይፋ ከህዝቡ ወገን መሆኑን አረጋገጠ ነው፡፡ በአድርባዩ ድርጅቶች ሥር ተደራጅቶ የነበረው ሃቀኛ ታጋይ በአንፃሩ አይነት ሁኔታ ከላይ መሪዎቹ በሚያካሂዱት የሥልጣን ሽኩቻ ምክንያት እሱም እየተመታ ቢሄድ ሙሉ በሙሉ ግራ መጋባት ምንም የሚያስገርም አይደለም፡፡ ግራ መጋባት ብቻ ባይሆን ለዚህ ክፍል ትግልም ልዩ ጥል በል አስቸጋሪ ሁኔታ ላይ ነው፡፡ የአድርባዮቹ ድርጅቶች አመራሮች ያስጨበጡትን የከሠረ የፖለቲካ መሥመር ይዞ ወደ ህዝቡ ሊሄድና ሊያደራጅ አይችልም፡፡ ያለው አማራጭ ሃቀኛውን መሥመር አንሥቶ የህዝቡን እንገብጋቢ ጥያቄዎች ይዞ ከሌሎች አብዮታውያን ጋር በአንድነት መቆም ብቻ ቢሆንም ይህ በአድርባዩ ድርጅቶች ውስጥ የነበረው የሃቀኛ ታጋዮች ክፍል ከፀረ ህዝብ ሃይሎች በኩል በወረደበት

ጭብአ ገና ገራ ከማገባት ደረጃ አለፍ፤ በወዠገበር ውስጥ ከመጥዞ አለፍ አለ ሂደም:: በዚህም የተነሣ ዛሬ በተለይ "በወዝአደር ሊግ" ውስጥ ተከለፈው የነበሩ ታጋዮች ብቻ ሳይሆኑ በአብዮታዊ በደድ በራሱ ውስጥ የሚገኙት ሃቀኛ ማርክሲስት ሌኒኒስቶች በአመራር ሰህተትና አድርባይነት ከኃጠማቸው የፖለቲካ ከሥረት ጋር ከፍተኛ ድርጅታዊ ከስረት ውስጥ ወድቀው ይገኛሉ::

ከዚህ ሌላ አንገኙህ የማንከደው የመኢሶን ድርጅታዊ መድከም አለ:: በሺህ የሚቆጠሩ አባላቱ ታሥረውበት፤ በመቶ የሚቆጠሩ አባላቱ በያለበት ወድቀውበት አንኳን አንደና ዓይነቱ ለጋ ድርጅት ይቅርና ግንም ድርጅት ቢሆን መትከሙ አይቀርም:: ነገር ግን ሁለት ነገሮች አሉ:: መኢሶን የሚከተለው መሥመር ሕዝባዊ በለሆነ ምንጊዜም ቢሆን ድርጅታዊ ኪሣራና መበተን ሊደርስበት አይችልም:: ይከንን ደግሞ ባለፈው አንድ ዓመት ተኩል የአብዮታችን ሂደት በሚገባ አሳይቶታል:: አሳሱ የቀኝ ኃይሎች ሕብረት በአድርባይ ድርጅቶች "ግንባር ቀደምነት" በመፈክሪያ መኢሶንን ከሕዝቡ ለመነጠል ሞከረ:: የመሥመር ትግል ብሎ የጀመረው የራሱን ኪሣራ ማጋለጫ ሆነ:: መኢሶንን ከሕዝብ የመነጠሉ ፖለቲካ አልሠራም:: ድርጅቱን ለመከፋፈል ሞከረ:: ለዚ አሁን "ከወዝአደር ሊግ" ድርጅት ላይና ሰሞከር እንደሚታየው በሰደም ውስጥ "ገራ ከንፍና" ቀኝ ክንፍ አያለ አንደጀመረው ሰዴሃሬው ቢሮክራቢ በመኢሶንም ውስጥ "ገራ ክንፍ" አገኝሁ ብሎ ቀለምደ ነበር:: "ገራ ክንፍ" የተባለችው ነገር አንኳን ክንፍ ሊተምላ ቀርቶ በሰተዋገ በኩል የረገፈች የታሪክ አተላ ሳብ ሆና ተገኘለች:: ይቺ "ገራ" ክንፍ ቢላት ቢላት ከአስር ሰው አለበለጠችለትም:: ማንገም አላተለለችለትም:: አንገኙህ ይከ አልሠራ ቢል በድርጅቱ ላይ በለየለት ፀረ ሕዝብ አመጽ ተሰማራ:: ከላይ አንገለነው በዚህ አመጽ የተነሣ ጉዳና ቂያችን ተጓከመ:: ግን አልተደመሰሰም:: በፖለቲካው አገላር በሃቀ ለአብዮቱ፤ ለሕዝቡ፤ ለእናት አገር ባደረገው ምርጫ አስከመጨረሻ የሚሰዋ ድርጅት መሆኑን በሰፊው ሕዝብ ፊት አስመሰከረ:: በነዚህ ጓዶች ደምና መከራ መኢሶን የሚጽፈው የትግል ታሪክ በሕዝብ ዘንድ ተቀባይነትን ጨመረለት:: በድርጅታዊ ትግባራ በኩል ደግሞ ለዘላቂው ትግሉ በውድ ጓዶቹ ደምና መከራ አያከፈለ የቀሰማቸውን ትምህርቶች በሚገባ አቀሀደ በአብዮቱ ሠፈር መታገሉን ቀጠለ::

ነገር ግን የኢትዮጵያ አብዮት በመኢሶን ግንባር ቀደም ታጋዮች ትከሻ ላይ ብቻ የወደቀ ኃላፊነት ብቻ አይደለም:: ዋናው ኃይል በሚሊዮን የሚቆጠረው የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው:: ይህንን ኃይል ለማንቀሳቀስ ደግሞ ብቻ ሳይሆን በግንባር ቀደምነት የተሰለፉ የኢትዮጵያ ማርክሲስት ሌኒኒስቶች፤ ላብአደሮችና አገር ወዳዶች ተግባር መሆኑን አያጋዓጉ ሃቀኛ ኢትዮጵያዊ፤ አያጋጓጉ ሃቀኛ ኢትዮጵያዊት አምነው መቀበል አለባቸው:: ለላብአደሩ፤ ለአኩልነት፤ ለብሄራዊ ነፃነት የቆሙ ኃይሎች ሁሉ ዛሬ ከመቼውም ጊዜ ይበልጥ የወደፊትን ግንባር ተወጥተው፤ የፀረ ሕዝቦች አመጽም ሆነ የተለያዩ አድርባይ አመራሮች የከበረ የፖለቲካ መሥመር ዕምቧቸውን ወበታትን ስሽንፈው በሃቀኛ መሥመር ላይ ለእናት አገርና ለአብዮት በሀብረት መቆም አለባቸው::

የዛሬው፤ የመኢሶን የሀብረት ጥሪ ይኸ ነው:: ወዝገበር ይበቃ፤ መበታተን ይበቃ፤ ከሁሉ በፊት ለአብዮታችን፤ ከሁሉ በፊት ለእናት አገራችን የምንል ኢትዮጵያዊያን ሁሉ አብ ለአብ ተያይዘን ወደፊት አንራመድ ይላል:: አንባቢ ይከንን ሊሳ የተራማጆች ጥሪ ስናስተጋባ "ኢማሌድህ" ብሎ ይጠይቀን ይሆናል:: በ?ፋ ከመፍረሱም በፊት ቢሆን "የወዝአደሩ ጋር ትገስ" እየተባለ ይተረተለት የነበረው "ኢማሌድህ" የየካቲት 1969 ዓ.ም. "ኢማሌድህ" አልነበረም:: ከዚያናው ጋር ሲነጻጸር ከላይ አንደጠቀምነው "ኢማሌድህ" ይባል የነበረው "ህብረት" ጥንድ ኪሣራዎች ደርሰበታል::

የመጀመሪያው የ"ኢማሌድህ" የፖለቲካ ከሥረት ነው:: አንዱ ድርጅት መቼም ራሱ ማርክሲስት ሌኒኒስት ነኝ በላሉ ብቻ "ማርክሲስት ሌኒኒስት" ነው ማለት አይቻልም:: በኢማሌድህ የፖለቲካ ከሰረት ከውጤቱ ተሩ ከተባሉት ድርጅቶች የፖለቲካ ከሰረት ጋር የተያያዘ ነው:: ይከንን ከሰረታቸውን ለማሳየት ሌላ ዝብዝብ ውስጥ ከመግባት እነዚህ "ማርክሲስቶች" "ይከ ዝቅተኛው ነው ከዚህ አለፈን አንሂዳለን" ይሉት የነበረውን የኢትዮጵያ ብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም እንዴት አድርገው ምንጠርጠሩን አንዳወጡት መጠቆም፤ ከዚያስ ወዲህ የየካቲት 1969 ዓ.ም. የኢትዮጵያ ማርክሲስት ሌኒኒስት ድርጅቶች ህብረት የጋራ መግለጫና መርሃ ግብር ላይ ከማሉበትና ከተገዘቱበት አቋማቸው የትናውን አንዳከበሩ ራሱን መጠየቅ ብቻ ይበቃል::

ሌላው ደግሞ ኢማሌድህ ላይ የደረሰው ድርጅታዊ ከሰረት ነው:: ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ኢማሌድህ የሚባለው ነገር የቱ ላይ "የድርጅቶች ህብረት" አንደሚባል ገራ የሚያጋባ ነበር:: መኢሶን አንደሆነ "ተባረረ" ኢጭአት አንደሆነ "ለጊዜው" ተወገደ፤ "የወዝአደር ሊግ" አንደሆነ የስዴሃሬው ቢሮክራቢ ሹማምንት "ገራ ክንፍ" ብለው አመራሩን ከያዙ በኋላና ሰጥቶ ሁሉ አቅሎፈሱ "በአስር ጤቶ ከታገሩ በኋላ ምን ቀርቶ ነዚህ "ህብረት አባል አንደሚሆን አይታወቅም:: አሳሱ የቀኝ ኃይሎች ህብረት በየካቲት 1969 ዓ.ም. የኢትዮጵያ አብዮታዊያን ለትግላቸው መሣሪያ አንዲሆናቸው በደማቸው ከፍለው ያቋቋሙትን "ኢማሌድህን" ማራቀቅን እዚህ ላይ አላቆም:: ሰዴሃሬው ቢሮክራቢ ለደርጉ ራሱንም ቢሆን የሚፈለገው በአብዮቱ ስም አየማለ ለሚያደርገው ጥፍጠፋ "ሽፋን" አስከለጠው ነው አንጂ ተራማጅን "ከደረሰ" በኋላ ምን ሊያደርግለት "አሹራራ" ይለዋል? በዚህም የተነሣ ሰዴሃሬው ቢሮክ



ራቢ "ዘመቻውን" የጥሉ አሁን ደግሞ "ሰደድም በሰዴሃሬዎች የተጥለቀለቀ ድርጅት ነው" በማለት በዚያ ውስጥ ያሉ ሃቀኞችን አየመታ ያፈራርሰው ይዟል:: አሁን የነወዝ ሊግ ድርጅታዊ ኪሣራ አየወደቀበት ነው::

በከሣራ ድርጅቶች "አባላት" የተመሠረተ "ህብረት" ደምሩ ያው ኪሣራ በመሆኑ ይከው በየካቲት ወር 1971 ዓ.ም. የወጣው "የህብረት ድምጽ" ህብረት መፍረሱን፤ "ኢማሌድህ" ይባል የነበረው ነገር ራሱ "በሰዴሃሬያን ስለተጥለቀለቀ" ከአንገኙህ አሱን "አየሀደ" ጋር ቱ ማቋቋም የማይቻል መሆኑን አበሰርልናል:: ለሰዴሃሬዎች "የኢማሌድህ ታሪካዊ ሚና" አለቀ ማለት ነው:: ከአንገኙህ በሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮትን በይፋ ከደው፤ ቢያገስ በዚህ ፕሮግራም ላይ የሚታገሉ ድርጅቶችንም ሆነ ግለሰቦችን በይፋ ተደፍጠው የሚታገሉበት በፀረ ሕዝብ ገጸታቸው ደፍረው የሚወጡበት ደረጃ አየደረሱ ነው ማለት ነው:: የየካቲት 1971 የህብረት ድምጽ ይህንን በፀረ አብዮት ጉዳና ላይ የተደረገ አንዱ "የወደፊት እርምጃ" አዲስ ምዕራፍ ብሎ በደምቃል::

ይህ "አዲስና ዉብ ምዕራፍ" የኢትዮጵያ ወዝአደሮች ጋር ቱ "ከድርጅቶች ውህደት" ሳይሆን "ከግለሰብ ከሙኒስቶች ውህደት" ይመሠረታል ብሎ የኢማሌድህንም ሆነ አዉሰው ቀር ተናል ይሉ የነበረቱን ድርጅቶች መፍረስ አበሰረል:: በዚህ "ሂደት" ታሪክ ላይ ወደፊት በሰፊው አንመለሳለን:: ይህ "አዲሱ ምዕራፍ" በከሠረ ፖለቲካ ላይ መጓዝ ጀምሮ የነበረው "ኢማሌድህ" ራሱም "ወደወዝአደር ጋር ቲነት" በመለወጥ ሳይሆን አንጻሩ በመበተን ወደ ታሪክ ትብያ መጣያ የወረደበት ምዕራፍ መሆኑን ብቻ ጠቁመን ለጊዜው አናልፈዋለን::

አንገኙህ የቀደመው ኢማሌድህ ከሠረ:: ፈርሷልም:: ነገር ግን ይከ ብቻ አይደለም:: ይህ ከሠረት ባይኖር አንኳን ኖሮ ኢማሌድህ "የማርክሲስት ሌኒኒስቶች" ብቻ ስለነበር ላብአደሮችንና አገር ወዳጆችን የሚጨምር ህብረት አልነበረም:: ዛሬ ከመቼውም ጊዜ የኢትዮጵያ አብዮት በቀኝ ኃይሎች ህብረት ሴራ የተነሳ ከገባበት መጥቀ ወጥቶ ወደፊት አንዲጓዝ የማርክሲስት ሌኒኒስቶች ብቻ ሳይሆን የመቀሳሳው የተራማጅ ኃይሎች ህብረት ያስፈልጋል:: ዛሬ መኢሶን ከላይ በቀረበው የጊዜው ሁኔታዎች ትንተናዎች ላይ ተመርኩዞ ለዚህ ህብረት ጥሪ ያደርጋል::

## ክፍል 2. የመላ ኢትዮጵያ ሶሸሊስት ንቅናቄ ለመላ ኢትዮጵያ ማርክሲስት ሌኒኒስቶች፤ ላብአደሮች፤ አገር ወዳጆች ሁሉ የትግል አንድነት ጥሪ

ጓዶች፤ ጓዲቶች፤ ወገኖቻችንና እህቶቻችን!

የመላ ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ የሰፊው ሕዝብ ወገን መርጦ ለአብዮታችንና ለእናት አገራችን ክብርና ነፃነት በግንባር ቀደምነት ሲዋደቅ የቆየና አሁንም በመዋደቅ፤ በመስዋትና ወደፊት በመራመድ ላይ መሆኑን ወዳጅ በደስታ ጠላት በመርበትበት የሚመሰክሩት ሃቅ ነው:: ቀደም ሲል በጥለማው በኃይለ ስላሴ ፋሽስታዊ አገዛዝ፤ ከዚያም በየካቲት የዲሞክራሲያዊ አብዮት ፍንዳታ ወቅት የሰፊውን የኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል ፈር ለማስያዝ ከሌሎች ታጋይ ኢትዮጵያዊያን ጋር ተሰልፎ ለአብዮቱ የእናት አገር ፍቅሩ የጠየቀውን ማናቸውንም መስዋዕትነት እየከፈለ በግንባር ቀደምነት ተሰልፎ ቆይቷል፤ አሁንም እንደ ተሰለፈ ይገኛል:: በዚህ ትግሉ በኢትዮጵያ አብዮት ላይ ተራ በተራ የተነሱ ኃይሎች ሁሉ ከተራ ፈውላል አሉባልታና ሃሜት አንስቶ አስከለየለት ፀረ ሕዝብ አመጽ ድረስ በማፈራረቅ መኢሶንም ላይ ተነስተው ሊያጠፉት ሞክረዋል:: ደግመን አንገልፃለን የመኢሶን የፖለቲካ አቋሞች የመላ ኢትዮጵያን ሕዝብ ፍላጎቶችና ምኞቶች የሚያንፀባርቁ፤ የሃገራችንን ክብር፤ አንድነቷንና በለጸገና ቀጣፊት፤ የሚያረጋግጡ አቋሞች በለሆኑ ማንኛውም ፀረ ሕዝብ ኃይል መኢሶንን በሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ፊት፤ በግንባር ቀደም ኢትዮጵያዊያን ፊት በፖለቲካ መሥመሩ ሊያጋልጠውና ሊያሳከመው አልቻለም:: በለሆነም የኢትዮጵያ አብዮት በመቼውም የተነሱ ኃይሎች በሃቀኛ ተራማጆች ላይ በፀረ ሕዝብ አመጽ ከመሠማራት በስተቀር ያገኙት የአብዮቱን ሂደት መቋቋሚያ ዘዴ የለም::

ፀረ ሕዝብ ኃይሎች በተለይ ከሁለት ዓመት ወዲህ በአብዮቱ ላይ ያካሄዱት የጥፋት ዘመቻ በመጠነም ቢሆን ለጊዜውም ቢሆን የአብዮቱን ሰፈር ማዳከም የቻለው ተራማጆች መከፋፈል በመቻላቸው ብቻ ሳይሆን በኢትዮጵያ ገራ ኃይል ወቅላነት ተጠቅመው አንዱን በአንዱ ለመምታት ያደረጉት ጥረት በለተሳካላቸው ነው:: ሠፈራችንን ያስጠቃው ለከፋፋዮች ሴራ ድርጅታችንን ሰጥተን በመገኘታችን ነው:: ከዚህ ሁኔታ ሊያወጣን የሚችለው በመሃከላችን መከፋፈልን አስፍተን ለፀረ ሕዝቦች መግቢያ ቀዳዳ በንነስ ብቻ ነው::

"ይከፋፈል ይበቃ" በንል ባሁን ወቅት ሁሉ አንደመኢሶን ያስቡ፤ ሁሉ የእኛን መሥመር ሙሉ በሙሉ ይከተሉ ማለታችን አይደለም:: ለኢትዮጵያ አብዮትና በሄራዊ ነፃነት በቆሙ የተለጠጠሩ ኃይሎች መካከል ብዙ ልዩነቶች አሉ:: ወደፊትም ይኖራሉ:: ነገር ግን ከእነዚህ ልዩነቶች በላቀግር የአብዮቱን ሠፈር የሚያያይዙ አንጋን መሠረታዊ የሆኑ ነገሮች አሉ:: መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ዲሞክራሲን ይፈልጋል:: በመላ ኢትዮጵያ የብሄረሰቦች እኩልነት ይጠይቃል:: የአገራችን ብሄራዊ ነፃነትና ክብር አይደፈር ይላል... በጥሩ በብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም ላይ የተጠቀሱት ዓላማዎች ሁሉ ሙሉ በሙሉ ከሥራ ላይ አንዲውሉ ...

ይጠይቃል፡፡ በነዚህ ዓላማዎች የምንስማማ ኃይሎች ሁሉ መሠረታዊ አንድነቶች አሉን፡፡ በነሱ ላይ ተመርኩዘን እነሱን ከሥራ ላይ ለማዋል በአንድነት ወደፊት መጓዝ አለብን፡፡ ይህ ፕሮግራም ከሥራ ላይ በሚውልበት ዘዴ በመሃከላችን ልዩነቶች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ ግን እነዚህ በአብዮት ወገኖች መሃከል ያሉ ልዩነቶች ናቸው፡፡ እኩልነት፣ አንድነት፣ ብልጽግና፣ ብሄራዊ ክብር እስከበለን ድረስ፣ ለነዚህ ዓላማዎች በሃቅ እስከቆምን ድረስ የኢትዮጵያ አብዮትና ብሄራዊ ነጻነት ጠላቶች በኛ መሃከል ምንም ልዩነት አያዩም! ለፀረ ሕዝብ ዓላማቸው እንዲያመቹ ቅድመ ተከተል ይሰጡታል እንጂ ዘር ዘር ለማውደም የሚፈልጉት አብዮትና እናት አገር የሚለውንና ለፀረ ሕዝብ ፖለቲካቸው አለገዛደም የሚለውን ነገር ቀድሞ ኃይል ሁሉ ነው፡፡

መኢሶን ለመላ ኢትዮጵያ ተራማጆች ዛሬ የሚያደርገው ጥሪ ከሁሉ አስቀድመን ይህንን ሃቅ ተገንዝበን ፀረ ሕዝቦች አንዱን ከሌላው እያጋጩ፣ አንዱን ለመምታት በሌላው እየተጠቀሙ ሁላችንንም ተራ በተራ ለማውደም ለስነዘረት ቢራ መሣሪያ ከመሆን እንዲቆጠቡ ነው፡፡ ሁለተኛ ልዩነቶች እንደሁኔታው አመቺነት በይፋ ወይም በህቡዕ ሃቀኛ ውይይቶችን እንድናንደምርና የትግል አንድነታችንን በተወሰኑ ቋሚ የትግል መስኮች ላይ እንደገና መገንባት እንድንጀምር ነው፡፡

1. ከሁሉ መጀመሪያ መኢሶን የሚያቀርበው ጥሪ ለፀረ ሕዝቦች መሣሪያነት ይብቃ! የሚል ጥሪ ነው፡፡ ዛሬ የኢትዮጵያ ተራማጆች ይከተሉ ያሉ በገፍ ቢታሠሩ፣ ቢሰቃዩና ቢረሸኑ ለዚህ ሁኔታ ተጠያቂው ደርግ ብቻውን እንዳይደለ ግልጽ ነው፡፡ የአድርባይ ድርጅቶች መሪዎች የኢትዮጵያን አብዮት ለፍርፋሪ በመሸጥ፣ ከአባሎቻቸው አንዳንዶቹ ደግሞ በዚህ በተባባሪ አመራር በመወናበድ ብዙ የመኢሶን ጓዶችን ብቻ ሳይሆን ዲሞክራቶችንና አገር ወዳዶችን ለጠላት እያባለሉ ሰጥተዋል፡፡ ይህ እነዚህን ኃይሎች በታሪክ ፊት ቢያስጠይቃቸው ምክንያት የለውም፡፡ መኢሶን አባላት "ማርክሲስት ሌኒኒስት አይደላችሁም" ቢባሉ እንኳን ቢያገኙ ቢያገኙ በብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት መድረክ ላይ የቆሙ ፀረ ፊውዳል ፀረ ኢምፔሪያሊስትና ፀረ ቢሮክራሲያዊ ካፒታሊስት ኃይሎች ናቸው፡፡ ስለሆነም የአድርባይ ድርጅቶች መሪዎች ከመኢሶን ጋር ያለው ልዩነት በሁለተኛ ደረጃ የሚታይ በአብዮት ሠፈር ያለ ልዩነት መሆኑን እያወቁ ይህ ቅራኔ በውይይት ሳይሆን በእሥራትና በርሸና እንዲፈታ መወትወታቸው ውጤቱም የአብዮቱን ሰፈር እያደከመ የፀረ አብዮትን ሠፈር የሚያጠናክር መሆኑ በነዚህ ድርጅቶች በራሳቸው ውስጥ ለሚገኙ ሃቀኛ ታጋዮችም መቃብር መቆፈር እንደሆነ ዛሬ በአቋራጭ በፈረሱት ድርጅቶች ውስጥ ተሰልፈው ይታገሉ የነበሩት ተራማጆች የወደቁበት ዕድል የማያጠራጥር ማስረጃ ነው፡፡ አንዳንዱ ተራማጅ አውቆም ሆነ ሳያውቅ የብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም ጠላት አድርጎ ከሰወሰናቸው ኃይሎች አንዱ ግለሰብ እንኳን ለፀረ ሕዝቦች ቢጠቁምና አሳልፎ ሲሰጥ ለኢትዮጵያ ተራማጆች ሠፈር መዳከም አስፋፊ አስተዋጽኦ ማድረጉ፣ ሕብረታቸው እንዳይመሠረት ተጨማሪ የጥላቻና የጥርጣሬ ግንብ ለመገንባት ማገዙና ዘር ዘር ደግሞ ፀረ ሕዝቦችን ለማጠናከር የራሱን መቃብር መቆፈሩ እንደሆነ መገንዘብ ይኖርበታል፡፡ በተቃራኒው ደግሞ አንዳንዱ ተራማጅ ሌላ ተራማጅ ላይ ፀረ ሕዝቦች ሊሰነዝሩ ለሚችሉት አመጽ ከመተባበር ሆነ ብሎ ሲቆጠብ የአብዮቱ ሰፈር እንዳይዳከም የሚፈለገውን አስተዋጽኦ ከማድረጉ በላይ በፀረ ሕዝቦች ቢራ በመፍረክረክ ላይ ያለው የተራማጆች አንድነት መልሶ እንዲያንሰራራ በቅድሚያ ለሚያስፈልገው መተማመን፣ መተባበርና በጋራ ጠላት ፊት በአንድነት የመቆም ስሜት እንዲዳብር ማድረጉ ስለሆነ አንዱን ጓድ ወይም ጓዲት ከሞት አድኖ አሉፍ የሚሄድ ወደር የሌለው አስተዋጽኦ አደረገ ማለት ነው፡፡

በዚህ የተነሳ ነው ዛሬ መኢሶን ለተራማጆች ህብረት መሠረት ለመጣል ይህ የመተማመን፣ የመተባበር፣ የወገናዊነት ስሜት በመሃከላችን እንዲሰፍን ከሁሉ አስቀድሞ ይህ የጥቆማ ወረርሽኝ፣ ይህ በኢትዮጵያ ግራ ወቀሳነት የተነሳ ስፍር ቁጥር የሌላቸው ጓዶች መስዋዕትነት የጠየቀን ወረርሽኝ ከመሃከላችን ወርሶ መነቀል አለበት የሚለው፡፡ ለዚህ ነው ለፀረ ሕዝቦች መሣሪያነት ይብቃ! ብሎ የሚያስተጋባው፡፡

ከዚህ ጋር የተያያዘ ሌላም የመላ ኢትዮጵያ ተራማጆች ተግባር መሆን ያለበት ጉዳይ አለ፡፡ ዛሬ በደርግ እሥር ቤቶች በመሰቃየት ላይ የሚገኙት በሺህ የሚቆጠሩት የመኢሶን አባላትም ሆኑ የሌሎች ማርክሲስት ሌኒኒስት ድርጅቶች አባላት፣ እንደዚሁም ስፍር ቁጥር የሌላቸው ዲሞክራቶችና አገር ወዳዶች በሙሉ በብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት መድረክ ላይ የቆሙ የአብዮቱ ኃይሎች ስለሆኑ በአስቸኳይ እንዲፈቱና አብዮታዊ ትግላቸውን እንዲቀጥሉ ተራማጆች ሁሉ ትግላቸውን ማስተባበር አለባቸው፡፡

2. በልዩነቶቻችን ላይ እንወያይ !

ይህ ጥሪ "እንደአጣዳፊ ተግባር" ተብሎ መቅረቡ ራሱ አድሃሪያዎች በኢትዮጵያ ተራማጆች መሃከል የነዙት የጥላቻና ያለመተማመን መርዝ ምን ያህል ፍሬ እንደሰጠ የሚያሳይ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ተራማጆች ወቅሳነትም የሚለካበት ማሣሪያ ነው፡፡ በተራማጆች ሰፈር በተለይ በሁለት ዓመት ውስጥ ፀረ ሕዝቦች ሆነ ብለው ያስፋፉት ይህ መርዝ በልዩነቶች ላይ እንኳን በጥሞናና በርጋታ መካሄድ ያለበትን ውይይት አፍኖት ይገኛል፡፡ ፀረ ሕዝቦች ከውይይት መግባባት፣ ከመግባባት አንድነት፣ ከአንድነት ደግሞ ድል እንደሚገኝ ያውቃሉ፡፡ ስለዚህ ይህ



ውይይት እንዳይካሄድ በገኙት ተንኮል ሁሉ ይጠቀማሉ፡፡ ዲሞክራሲያዊ መብቶችን አፍነው መያዛቸው እንኳ ምክንያት በዲሞክራሲያዊ ውይይት ከሚደርስባቸው መጋለጥ ለመዳንና በተራማጆች ሰፈር በሃቀኛ መሥመር ላይ የተመረኮዘ አንድነት እንዳይኖር ለማድረግ እንደሆነ ግልፅ ነው፡፡ አብዮታዊያን ግን "ዲሞክራሲ የሌለና ምን ይደረጋል ውይይት አይቻልም" ብለው ዝም አይሉም፡፡ በልዩነቶች ላይ መረዳዳት ለአብዮቱ ሂደት ምን ያህል ጠቃሚ እንደሆነ በመረዳት ይህ ውይይት እንዲኖር ያለማቋረጥ መታገል አለባቸው፡፡

ነገር ግን ይኸንን ውይይት የሚፈሩ የሚሰጉቸው ፀረ ህዝቦች ብቻ አይደሉም፡፡ የአድርባይ ድርጅቶች መሪዎች በዚህም በኩል አሳፋሪ የሆነ ተልእኮአቸውን ቢያካሂዱ ቆይተዋል፡፡ ካለፈው ስህተታቸው ምንም ትምህርት ያልቀሰሙ አንዳንድ የ"ግራ" አድርባዮች አሁንም ቅሪቶች ዕጣቸው በሃቀኛ አብዮታዊ መሥመር ላይ እንዳይሰለፍ ውይይትን ለማፈን ቀድሞ በመሰሪያ የተሰለፉትን ያህል ዛሬ ደግሞ በተለይ በዕጣቸው ጠቅላነት በመጠቀም፣ የቆየ ጥላቻና መጠራጠር እንዳይጠፋ ለማድረግ እየሞከሩ ናቸው፡፡ ቀደም ቢልም በሆነ የኢህአፓ መሪዎች ሃቀኛው ተከታዮቻቸው ነገሩ ገብቶት ዐደአብዮቱ ሰፈር እንዳይደበለቁባቸው ሲሉ ውይይትን ለማፈን "አታንብቡ አትመራመሩ" ብቻ ባይሆን "ከፋሺስቶች ጋር አትሮጡ እነርሱ አይቻሉም ያዐናብዷችኋል" ይሉ እንደነበር እናረበውም፡፡ ዛሬም በሆነ የቀኝ ሃይሎች ህብረትና አድሀሪ ቱልቱላዎች "ከመኢሶን ጋር ያለን ልዩነት በውይይት ሊፈታ የሚችል አይደለም" በለው ሲዘበርቁ የሚያባቸው ቀድሞ ኢህአፓ ያበየው የነበረውን የአብዮታዊ መሥመር ፍራቻ ብቻ ባይሆን ዲሞክራሲን አፍነው በደረቅና አስልቺ ቅስቀሳቸው ህዝቡን አደናቀረው በጠመንጃ አፈሙዝ ለዘላለም ለመግዛት ያላቸውን ምኞትም ነው፡፡ ይህ ፖለቲካቸው በኢትዮጵያ ተራማጆች መካከል ስለሉት ልዩነቶች ከ"ግራ" አድርባዮች ጋር የተደረገውን ያህል እንኳን ምንም አይነት የረባ ውይይት እንዳይካሄድ አድርጓል፡፡ በዚህም የተነሣ የአብዮቱ ሰፈር አባል የሆኑት ሃይሎች ተራ በተራ እንዲመቱና እንዲዳከሙ ተደርጓል፡፡

ከዚህ አሳዛኝ ሁኔታ ለመውጣት ለኢትዮጵያ ብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት በተሰለፉ ሃይሎች መካከል ከመቸ በይፋ፣ ካሰመቸ ደግሞ በህቡዕ ውይይት ያስፈልጋል ስንል የውይይት ነጥቦች ምን ምን መሆን አለባቸው?

የመጀመሪያው የውይይት ነጥብ ዛሬ ለፀረ ህዝቦች አመፅ ተጋልጠው በየእሥር ቤቱ የሚማቅቁት የመኢሶን፣ የኢጭአት፣ የዐዝአደር ሊግ፣ የአብዮታዊ ሰደድ፣ የማሌሪድ አባላት፣ ሌሎች ዲሞክራቶችና አገር ወዳዶች፣ እንዲሁም በኢህአፓ ውስጥ አብዮታዊ መስመር ይከተሉ የነበሩ የጀብደኛ አመራራቸውን ጭፍቅነትና የቀለበሽ መሥመራቸውን ከሃሰነት በርግጥ የተረዱ ተሰናብደው የነበሩ ሃቀኞች ጭምር— እንደአብዮቱ ጠላቶች የሚቆጠሩ ሃይሎች ናቸው ወይስ አይደሉም የሚለው ጥያቄ ነው፡፡ መኢሶን እነዚህ ጓዶች የአብዮት ጠላት አይደሉም እንዲያውም ዛሬ በፀረ ህዝብ ሃይሎች እጅ ግፍና መከራ በመቀበል ላይ ያሉት በሃቅ ለብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት የቆሙና ሊቆሙ የሚችሉ ዐገኞች በመሆናቸው ነው ይላል፡፡

እንኳን የሌላ ድርጅት አባላትን፣ እንኳን ያስተዳደራቸው ዴሞክራትና አገር ወዳድ ግለሰቦችን ቀርቶ በአንድ ድርጅታዊ መዋቅር ትብብር አብረዋቸው የተሰለፉትን ጓደኞቻቸውን የከዱና ለጠላት አጋልጠው የሰጡ እንዳንዱ አድርባይ "መሪዎች" በርግጥ ለዚህ መልሳቸው ይኸ ሁሉ በሽህ የሚቆጠር ታጋይ አብዮትን ከድቷል፣ ታጋይ የኢትዮጵያ ልጆች እኛ አተሳሰቹ ብቻ ነን፣

እንደሚሆን ግልፅ ነው:: ከዚህም "አስተባባሪ" ተነስተው በጠቅላላ በኢትዮጵያ ተራማጆች ላይ /በድርጅቶቻቸውም ውስጥ ባሉ ሃቀኞች ጭምር/ እሥራት፣ ጭፍጨፋው፣ ርሸናው እንዲቀጥል እንደሚገፋፉ የታወቀ ነው:: በዚሁ ነጥብ ላይ እርስ በእርሱም ይወያይ፣ ራሱን ይጠይቅ፣ ከሌሎች አብዮታውያንም ጋር ሃሳብ ይለዋወጥ የምንለው በድርጅቶች ውስጥ ያለውን ሃቀኛ አብዮታዊና ገና ያልተደራጀውን ማርክሲስት፣ ዴሞክራትና አገር ወዳዱን ነው:: ከማንኛውም የንዑስ ከበርቴ አስሀ፣ ከማንኛውም የቡድን ስሜት በራቀ መንፈስ፣ ከሁሉም በላይ ለኢትዮጵያ አብዮትና ለብሄራዊ ነፃነቷ በሚያረጋግጥ መንፈስ የሚካሄድ ውይይት መሆን ከሁለት ዓመት ጀምሮ የማጠቃለውን ዛሬ በተጨባጭ በሃገሪቱ የፖለቲካ መድረክ ላይ የተመሰከረውን ሃቅ አጉልቶ ያሳያል:: ይህ ሃቅ ሌላ ምንም ነገር ሳይሆን በብሄራዊ ዴሞክራሲያዊ አብዮት መድረክ ላይ ኅብር በሚታገሉ ሃይሎች መሀከል ያሉት ልዩነቶች በሁለተኛ ደረጃ የሚታዩ ልዩነቶች ናቸው የሚለው ሃቅ ነው:: ከዚች መሠረታዊ ሃቅ ላይ መድረስ ቢቻል ለመላ ኢትዮጵያ ተራማጆች አንድ ትልቅ የትግል አንድነት መድረክ ተከፈተ ለማለት ይቻላል:: ልዩነቶች በውይይት እንዲፈቱ፣ መጠቆም፣ ማሳደድ፣ ማሠር፣ መረሸን እንዲቆም የኢትዮጵያ ተራማጆች በሙሉ በአንድነት የሚታገሉበትን የአብዮቱ ባለቤት የሆነውን ሰፊ ህዝብ በአንድ ድንኳ የሚቀበቅቡበትና የሚታገሉበት የጋራ መድረክ አገኙ ማለት ነው:: ለአዲሱ የቀኝ ሃይሎች ህብረትና ለጠቅላላው የፀረ አብዮት ሃይሎች "የከፋፍለህ ግዛ" ሴራ አንድ ማርከዥ ተገኘ ማለት ነው::

ሌላ የውይይት ነጥብ ዛሬም እንደዛሬ ዓመቱ የዲሞክራሲ መብቶች ጉዳይ ለኢትዮጵያ አብዮት አንገብጋቢ ጉዳይ ነው ወይ? የሚለው ነጥብ ነው:: እዚህም ላይ የመኢሶንና የተቀፋት ሃቀኛ አብዮታውያን መልስ ግልፅ ነው:: እንዲያውም ባለፉት ሁለት ዓመታት በአብዮታችን ላይ ለደረሰው ጉዳት ሁሉ ለህዝባዊ ድርጅቶች መፈራረስም ሆነ ለቢሮክራሲው መንገስ፣ ለተራማጆች ህብረትም መንሸራሸሩ መውጣትም ሆነ ለአያንዳንዱ አብዮታዊ ድርጅት መዳከም፣ ለብሄረሰቦች የእኩልነት መብትም መረገጥ ሆነ ለኢትዮጵያ ህዝቦች ዴሞክራሲያዊ አንድነት ከፍተኛ አደጋ ላይ መውደቅ፣ የአብዮታችን እድል በርጥ ሃይሎች ቁጥጥር ስር መውደቅም ሆነ የኢትዮጵያ ብሄራዊ ነፃነት መደፈር፣ ለዚሁ ሁሉ አንዱ ምክንያት ይህ አንገብጋቢ ጉዳይ በወቅቱ ተገቢ መልሱን አለማግኘቱ ነው እንላለን:: በየድርጅቶቹ ቀገጣ ላይ ፊት ብለው በነበረ



አድርባዮች የተነሳ ተወናብዶ "ከቁ ዲሞክራሲ አለ" ቢል የነበረው ሃቀኛ ዛሬስ በሃገራችን የነገሠውን ፀረ ዲሞክራሲ ሲመለከት፣ በየድርጅቱ ውስጥም ሆነ ከዚያ ውጭ ባለው ሃቀኛ ዲሞክራትና አገር ወዳድ ላይ የሚደርሰው ግፍ በራሱ ላይ ሲደርስ ከተጨባጭ ሁኔታ የቀሰመው ትምህርት ምንድን ነው? እጅ ለእጅ ተያይዞ ለዲሞክራሲያዊ መብቶች መታገል፣ ለዚህም ዓላማ የአብዮቱ ባለቤት የሆነውን ሰፊ ሕዝብ በይፋም ሆነ በህቡዕ ማታገል ያስፈልጋል ወይስ አያስፈልገውም? ይኸም አንድ ሌላና ከፍተኛ የውይይት ነጥብ ነው::

ሶስተኛ ወሳ የኢትዮጵያ ተራማጆች ሊወያዩበት የሚገባው ነጥብ የብሄራዊ ነፃነታችንንና የሃገራችንን ክብር የሚመለከት ነጥብ ነው:: ከሰፊው ሕዝብ እየራቀና እሱን እየተቃረነ የተጠናከረው የቀኝ ኃይሎች ህብረት በሰፊው ሕዝብ ላይ መተማመን በመፍራቱ፣ እምነቱን በውጭ ኃይሎች ላይ መጣሉና በቀኝ ኃይሎች ህብረት ግብዣ በሺህ የሚቆጠሩ የባዕድ ወታደሮች ሃገራችን መጥተው መሥፈራቸው አብዮታችንን አራምደታል? ወይስ ወደኋላ ጎትቶታል? ለኢትዮጵያችንስ በአፍሪካም ሆነ በሌሎች የዓለም ሕዝቦች ፊት የነበራትን ዝናና ስም ወምርሳታል ወይስ ስሟንና ታሪኳን አጉድፎባታል? ራሷን የቻለች ኩሩ አገር አድርጓታል ወይስ የባዕድ ኃይሎች ተቀጢላ ሆናለች? መኢሶንና ሌሎች የኢትዮጵያ አብዮታዊያንና አገር ወዳዶች የቀኝ ኃይሎች ህብረት በውጭ ኃይሎች ተማምኖና በነሱ ድጋፍ ተጠናክሮ አብዮታችንን አሁን የሚገኝበት አስቸጋሪ ሁኔታ ላይ ጥሎታል፣ የውድ እናት አገራችንንም ክብር አዋርዶታል ይላሉ:: በአድርባይ የድርጅት መሪዎች አሉባልታ ተወናብዶና በጊዜው በኢትዮጵያ አብዮትና በሃገራችን ህልውና ላይ አፍጥጠው በነበሩት ከባድ ፈተናዎች ተማርኮ የመኢሶንን "ራስን በራስ መቻል" "እርዳታን በሁለተኛ ደረጃ መመልከት" "ለብሄራዊ ነፃነት ቀናተኛ መሆን" "ዕምነትን በ28 ሚሊዮኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ መጣል" የሚሉ መፈክሮች መረዳት አቅቶት የነበረው ሃቀኛ ታጋይ ዛሬ በሃገራችን ከሚያየውና ከሚሰማው ሁሉ ምን ተጨባጭ ትምህርት አገኘ? ዛሬ ካለንበት ማጥ ውስጥ ለመውጣት በነዚሁ መፈክሮች ስር ተሰልፎ ለአብዮታችንና ለእናት አገራችን ክብር የኢትዮጵያ ተራማጆችና አገር ወዳዶች ሁሉ እጅ ለእጅ ተያይዘን ማናቸውንም የውጭ ተጽእኖ መቋቋም አለብን:: ሰፊውንና በአገር ፍቅር ስሜቱ ዓለም ያደነቀውን የኢትዮጵያ ሕዝብ ትግሉን እንዲያፋፍም መቀስቀስ አለብን ወይስ የለብንም? ይኸም ሌላ የውይይት ነጥብ ነው::

አራተኛው የውይይት ነጥብ ሃቀኛውን የተራማጆች ህብረት የሚመለከት ነጥብ ነው:: ለሃቀኛ የተራማጆች ህብረት ዋናው እንቅፋት የአድሃሪዎችና የየስርጎገቦቻቸው መከፋፈል ሴራ፣ የአብዮታዊ ሰደድም ሆነ የሌሎች አድርባይ ድርጅቶች መሪዎች የስልጣን ጥም መሆኑ እየታወቀ ይህ ችግር በመኢሶን "አበጠ ራሱ ወደፓርቲ ለመለወጥ ፍላጎት" ሲለጠፍ ቆይቶ ነበር:: ዛሬ ይኸ ሁሉ በደልና ግፍ ደርሶበት አሁንም ለሃቀኛ ተራማጆች የሕብረት ጥሪ የሚያደርገው ማነው? ሲያሻቸው ድርጅቶችን እንዳለ በ "አቋሙ" ከተራማጆች ህብረት የሚሰርዙት፣ ሲያሻቸው በሌሎች ድርጅቶች ውስጥ ገብተው "ሰምበር" የሚያካሂዱት፣ ዘር ዘር ደግሞ አብጠውና ከአድሃሪው ቢሮክራሲ ተዋህደው ራሳቸውን ወደ "ወዛደር ፓርቲነት" ለመለወጥ ጥርጥር የሚሉት የኢትዮጵያ አብዮታዊያን ሃቀኛ ህብረት እንቅፋት እነማን ናቸው? የአብዮታዊ ሰደድ መሪዎች ወይስ መኢሶን? መኢሶን አሁንም ራሱን ብቻውን ወደፓርቲ የመለወጥ ሃሳብ የለውም፣ አሁንም ሃቀኛ ከሆኑ ማርክሲስት ሌኒኒስቶች ጋር ለመወያየት የአብዮቱን ሰፈር ከመበታተን ይልቅ ለመሰብሰብ ይታገላል:: የኢትዮጵያን አብዮታዊያን አንድነት የሚሻው ሃቀኛ ታጋይ ባለፈው አንድ ዓመት ተኩል ካየውና ከቀሰመው ተጨባጭ ትምህርት ተነስቶ የሚከተለው የትግል አቅጣጫ ምንድን ነው? እንደኛ ለጠንካራና ለዲሞክራሲያዊ አንድነት፣ እንደኛ ለሃቀኛ ዲሞክራሲያዊ ውይይት ይታገላል ወይስ አይታገልም? ከአድሃሪው ቢሮክራሲና ንዑስ ከበርቴው ተመራርተው በኢትዮጵያ ሕዝብ ትከሻ ላይ ፀረ ወዛደር የሆነ የዚያድ ባሬው ዓይነት "የወዛደር ፓርቲ" ሲጭኑ ዝም ብሎ ይመለከታል ወይስ ከሃቀኛ ማርክሲስት ሌኒኒስቶች ጋር ተባብሮ በወዛደሩ፣ በአርሶአደሩ፣ በመለዮ ለባሹና በአብዮታዊው ምሁር አካባቢ ባሉቸው መንገድ ሁሉ የሃቀኛውን የወዛደር ፓርቲ መሠረት ለመጣል በትጋትና በቆራጥነት፣ በዲሲፕሊንና በትዕግሥት ይሠራል? ይኸም አንድ የውይይት ነጥብ ነው::

በዚህ መልክ ብዙ የውይይት ነጥቦች እንደመንደርደሪያ ሆነው ሊቀርቡ ይችላሉ:: ዋናው ነጥብ አሁን እነዚህን ዘርዝሮ መጨረሱ ላይ አይደለም:: ዋናው ነጥብ የኢትዮጵያ ተራማጆች ካለፉት ስህተቶቻቸው አስፈላጊውን ትምህርት ቀስመው ከጨቅላነት በቶሎ ተላቅቀው ለፀረ ሕዝቦች መሣሪያነታቸውን ዛሬውኑ ማቆማቸውና በልዩነቶቻቸው ላይ በግልፅ ለመወያየት መወሰናቸው ነው:: ይህ እርምጃ ከተወሰደ ከነዚህ የመንደርደሪያ ነጥቦች ሌሎች ለኢትዮጵያ አብዮት መሠረታዊ የሆኑ ጥያቄዎች ይኖራሉ:: በየጊዜው ደግሞ ከተለዋዋጭ ሁኔታ ጋር አብረው የሚፈልቁ የመወያያ ነጥቦች ይኖራሉ::

ውይይቱ እንዴት ይካሄድ? ፀረ ሕዝብ ኃይሎች ይህ ውይይትና የሚያስከትለው መግባባት እንዳይኖር ዲሞክራሲያዊ መብቶችን አፍነው ይዘዋል:: በአብዮቱ አንገብጋቢ ጥያቄዎች ላይ ለየት ያለ አቋም ያለውን ሁሉ "ቀኝ መንገደኛ" "የቀኝ ክንፍ" "መኢሶን ሰርጎገብ" እያሉ ያሥራሉ፣ ይረሽናሉ:: ከዚህም በረቀቀ ዘዴ በተራማጆች መካከል ሊኖር የሚገባው መተማመን እንዳይኖር፣ ጥላቻ፣ ጥርጣሬና መከፋፈል እንዲነግሥ ሌት ተቀን ይሠራሉ:: እዚህና ዉ ወጥመዳቸው ውስጥ ካለወደቅን የዲሞክራሲያዊ መብቶች መታፈን የተራማጆችን መወያየትና

መቀራረብ ያጊትተ እንደሆነ እንኳ ጠርጠው አያፍኑም፡፡ ስለሆነም የሚተማመኑና የሚተቀ
ወቀ ተራማጆች ዛሬ ነገ ባይሉ ከላይ በጠቀስናቸውና በሌሎች እንገብጋቢ ብለው በሚያም
ኗቸው አርእስቶች ላይ በሀቡዕና በደቡገሊን የሚካሄዱ ውይይት ይጀምሩ እንላለን፡፡ በ
ገበሬ ማህበራት፣ በዐዘአደሩ አከባቢ፣ በቀበሌያች፣ በወጣቶች፣ በቢቶች፣ በመለዮ ለባ
ሹ ውስጥ፣ በዩሁራን፣ በአገር ወዳድና ዲሞክራት የጦርና የፖሊስ መኮንኖች አከባቢ በ
ሃቀኛነታቸው፣ በቁምነገረኛነታቸው፣ በምስጢረኛነታቸው፣ በሃገር ፍቅራቸው የሚተዋወቀ
ኢትዮጵያውያን ሁሉ በያሉበት አከባቢ እነዚህን የአብዮታችንንና የሃገራችንን እድል የ
ሚመለከቱ ጥያቄዎች እያነሱ በጥንቃቄ መወያየት ይጀምሩ፡፡ የመኢሶን አባላት በሙሉ ለ
ዚህ ውይይት ዝግጁ ናቸው፡፡

ከዚህ ከሃቀኞችና በሚተማመኑ ኢትዮጵያውያን መሀከል ከሚካሄዱ የመጀመሪያ ደረጃ
ውይይት አልፈን ለመሄድ መዘጋጀት አለብን፡፡ ይኸውም ድርጅት ለድርጅት መካሄድ ያለበ
ት ውይይት ነው፡፡ እርግጥ ከላይ እንዳልነው ዛሬ ቀደም ቢል የነበሩት ተራማጅ ድርጅ
ቶች አመራሮቻቸው በተከተሉት የከሰረ ፖለቲካ የተነሳ በመበታተን ላይ ናቸው፡፡ የከዓ
ውም ከድቷል፡፡ ከሃቀኛው ብዙ እየታፈሰ በየእስር ቤት ነው፡፡ ቢሆንም ምንም እንኳን
አመራሮቻቸው ቢከዱ ቅሉ የእነዚህ ድርጅቶች ሃቀኛ አባላት በቅድሚያ አስፈላጊውን ውይ
ይት በውስጣቸው ካካሄደው ሃይላቸውን በማሰባሰብና አደርጅተው በአድሃሪው ቢሮክራሲ የተ
ባነበቸውን አመራር ወዲያ ትተው ከሃቀኛ አብዮታውያን ጋር ከገለሰብ ውይይት አልፍ በ
ሚሄድ ደረጃ ውይይት ሊከፍቱ ይችላሉ፡፡ በዚህ ውስጣዊ ውይይት የሚደርሱበቸውን ሊያቀ
ርቧቸውና ውይይት ሊጋብዙበቸው ይችላሉ፡፡ በዚህም ደረጃ ቢሆን መኢሶን ከተራማጆች አ
ካባቢ በሚቀርቡ ትንተናዎች ላይ ተመርኩዞ ሃሳቡን ይገልጻል፡፡ ይህ በየድርጅቱ ውስጥ
የቀሩት ሃቀኞች በውስጣቸው የሚያካሂዱት ውይይት ከሌሎች ተራማጆች ጋር ከላይ በጠቀስነው
መሰከ በገለሰብ ደረጃ ከሚካሄደው ውይይት ጋር አይፃረርም፡፡ እንዲያውም ተጋግዘውና አብ
ረው ሊሄዱ የሚችሉ ናቸው፡፡

በሌላ ደረጃ ደግሞ በውጭ አገር ያሉ የተራማጅ ድርጅቶች አካሎች የሚቀኑ ብሄ
ረሰብ እንቅስቃሴዎች አካሎች፣ የተበታተኑ ተራማጆች፣ ዲሞክራቶችና አገር ወዳዶች እነ
ዲሁም የ"ገሬ"ና የቀኝ አድርባይ ድርጅቶች ደጋፊዎች የነበሩና ሃቀኛ ወገኖች፣ በተማ
ሪዎች ንቅናቄ አማካይነትም ሆነ ድርጅቶቻቸው በሚከፍቱላቸው መድረክ ሁሉ ሊያካሂዱት
የሚችሉት ጠቃሚ ውይይት አለ፡፡ እርግጥ አሁኑ የቀኝ ሃይሎች ህብረት በተለይ የኢትዮ
ጵያን ሰፊዎች የትግል [illegible] በአፈሙዝ ሃይል ያንበረከከ ከመሰለው በኋላ በውጭ ያለው
ንም ወቢትና አብዮታዊ ሃይል ሁሉ በልዩ ልዩ ተፅዕኖ ለመበታተንና ለማዳከም እየተረረ
መሆኑን እናውቃለን፡፡ ይሁንና በልዩ ልዩ ድርጅቶች ደጋፊዎችም ሆነ በጠቅላላው ለኢት
ዮጵያ አብዮት፣ ብሄራዊ ነፃነት በቆሙ ሃይሎች መሃከል ውይይት ለማካሄድ በአገር ውስ
ጥ [illegible] በመታገል ላይ ካለው ሃይል በውጭ አገር የሚገኙት የኢትዮጵያ ተራማጆች የተ
ሻለ እድል አላቸው፡፡ ይኸ የተለየ ሁኔታቸው በበኩላቸው አደራ ተጠቅመው ከሚኖሩትም



ቡድን ስሜት በላይ ለዚች እናት አገራችን ክብርና ነፃነት በቁርቁር [illegible] ተነሳስተ
ው፣ የተማሪ ማህበሮቻቸውም ሆኑ ድርጅቶቻቸው በሚከፍቱላቸው መድረክ አማካይነት ነፃና
ዲሞክራሲያዊ ውይይት እያካሄዱ፣ ለተራማጆች የትግል አንድነት ምባሌነት ያለው አስተዋፅ
ዖ ሊያደርጉ ይችላሉ ብለን እንገምታለን፡፡ በዚያም ያሉ የመኢሶን አባላትና ድርጅታዊ
አካሎች ለእንዲህ አይነቱ አብዮታዊ ተልእኮ ዝግጁ መሆን አለባቸው፡፡ ናቸውም፡፡

ውድ ጓደኞችና ጓዶች፣ ወንድሞችና እህቶች!

ለኢትዮጵያ ተራማጆች ህብረት ጥሪ ቢደረግ ከዚህ "ለጠላት መሣሪያነት ይብቃ"
"ተራማጆች.አንዐያይ" ከሚል ጥሪ አልፈን ለመሄድ ብንችል ኖሮ ምንኛ ደስ ባለን ነበር!
ነገር ግን ዛሬ ቀደም ቢል የነበሩት ተራማጅ ድርጅቶች ሁሉ ያሉበት የመፈራረስ ደረጃ፣
በተራማጆች መሀከል አድሃሪዎች የነዙት የጥርጣሬና የአለመተማመን ሁኔታ ቢታይ ዛሬ ጥሪ
ያችን ከነዚህ "የመጀመሪያ ደረጃ" ጥሪዎች አልፍ ሊሄድ ይችላል ወይ?? ዛሬ ባለነበት
ሁኔታ በነዚህ ሁለት ዝቅተኛ ነጥቦች ላይ አስቀድመን ባንስማማ፣ እነዚህን በሃቅ ከሥራ
ላይ ለማዋል ባንታገል፣ "ተራማጆች እንዲህ እንሥራ፣ እንዲያ እናድርግ" እያልን ከፍተ
ኛ መተማመንን ድርጅታዊ ቅንብርን የሚጠይቁ የጋር ተግባሮችን እንዘርዝር ብንል ሆድ ቢ
ያውቅ ደር ማታ አይሆንም ወይ?? ራስን ማታለል አይሆንም ወይ?? እና ይሆናል እንላለን፡፡
ስለዚህ ነው ይህ "እንደገና ለተራማጆች አንድነት ጥሪ" ብለን የበነዘርነው ጥሪያችን
ከነዚህ ሁለት መሠረታዊ ነገሮች አልፍ ሌላ "ተግባር" ውስጥ ዘርዝር መገባት ያልታየነ፡፡
አሁን ካለነበት ደረጃ ተነስተን እስቲ ለጠላት መሣሪያነት ይቁም፣ እስቲ በአብዮት ጥያ
ቄዎች ላይ ሁኔታው እንደሚፈቅደው በየደረጃው ውይይት ይጀመር! ይኸ ከሆነ በኋላ መኢሶን
አስፈላጊ ሆና ቢያገኘው ከዚህ አልፍ የሚሄድ ሌላ መርሀ ገብር፣ ሌላ የድርጊት ፕሮግራም
ያቀርባል፡፡ እንደሁኔታው፣ እንደተራማጆች አንድነት ሥር መሰደድ ታይቶ ይህ የጋራ መርሃ
ግብር ወይም የድርጊት ፕሮግራም በእርግጥ መኢሶን ብቻ ባይሆን የኢትዮጵያ ተራማጆች ተወ
ያይተው የሚስነዘሩት መርሃ ግብር ሊሆን የማይችልበት ምንም ምክንያት የለም!

ለማጠቃለል፣ ከላይ በሰፊው እንዳብራራነው ዛሬ በአገራችን ምንም ያህል ገፍና ጭ
ፍጨፋ በተራማጆች ላይ ቢወርድም ቅሉ ዝጠበጡ ሁኔታ የአብዮታውያንን አንድ ትክክለኛነት
ከእለት እለት እያጎላ እያበየ፣ የቀኝ ሃይሎች ህብረት ኪሣራና ክህደት ደግሞ እንደዚሁ
እያጋለጠ የሚሄድ አመቺ የፖለቲካ ሁኔታ አለ፡፡ በዚህ እንፃር አሁኑ የቀኝ ሃይሎች ህ
ብረትና የበላይ አዛዦች የኢትዮጵያ አብዮትም ሆነ ብሄራዊ ክብር ለሚያቀርቧቸው እንገብ
ጋቢ ጥያቄዎች ለእንዳቸውም ተገቢ መልስ ሊሰጡ ስለማይችሉ ከኪሣራ ኪሣራ፣ ከመጋለጥ መ
ጋለጥ እንጂ ካሁኑ የተሻለ እድል እንደማይገጥማቸው ባይታለም የተፈታ ጉዳይ ነው፡፡ በ
ዚህ ልክ ደግሞ ማንኛቸውም መስዋዕትነት እየከፈሉ በሃቅ ለአብዮትና ለእናት አገር ክብር
ለቆሙ ሃይሎች ጊዜው ይበልጥ እያመቻቸ ይሄዳል፡፡

ቢሆንም ኪሣራቸውን ለመሸፈን የተራማጅን ሰፈር ለማዳከም ፀረ ሕዝቦች በአብዮታዊያን ላይ ያወረዱት በታሪካችን ምንም ዓይነት ተወዳዳሪ የሌለው ገፍ የተነሳ ከዚህ በፖለቲካዊ አንጻር አዲስ አመቺነት ጋር የሚነጻጸር ድርጅታዊ ጥንካሬም ሆነ የተራማጆች አንድነት አለ ለማለት አይቻልም:: ነገ ይኸ ዘላቂነት የለውም:: በተለያዩ አድርባይ አመራሮች ከሥረት የተነሳ እርግጥ ዛሬ ብዙ ሃቀኞች ተስፋ በመቁረጥ፣ በመበታተን፣ ተደራጅተው መታገልን እርም ብለው በመተው ላይ ይገኛሉ:: ባይወደድ ባይነሳ፣ ተስፋ መቁረጥና እንደገና ማንሰራራት ባይ ፈረቀበት የመጨረሻውን ገኑን የመታ አብዮት በየትም አገር ታሪክ ታይቶ አይታወቅም:: ይህ ሁኔታ ለና አዲስ በመሰለም በብዙ አብዮቶች ታሪክ ተደጋግሞ የታየ ሁኔታ ነው:: ስለሆነም ዛሬ አድርባይ መሪዎቻቸው በተከተሉት የ[illegible] ፖለቲካ መሥመር የተነሳ ሕዝቡ የተፋቸው፣ ነገ ደግሞ በሃቀኝነታቸው የተነሳ በአድሃሪው ቢሮክራሲ ሙሉ ቁጥጥር ስር የወደቀው የቀን ኃይሎች ሀብረት የሚያሰድዳቸው ሰፍር ቁጥር የሌላቸው ገራ የተጋቡ ጓደኞችን አሉ:: እነዚህ ወገኖቻችን አንድ ነገር ማወቅ ይኖርባቸዋል:: ሰፍርቁሪ ተሸጠው ሰፊውን የኢትዮጵያ ሕዝብ የከዱት አድርባይ መሪዎቻቸው ለተከተሉት ፖለቲካ ዘላዓለማቸውን ሲሰቀቁ መኖር የለባቸውም:: በሃቅ ለሰፊው ሕዝብ የቆሙ ከሆኑ ለኢትዮጵያ አብዮትና በሄራዊ ክብር የሚደረገው ትግል ገና ከፊታችን ነው:: ያለፈውን ሁኔታ በጥሞና መርምረው፣ ከተፈጸሙ ስህተቶች አስፈላጊውን ትምህርት ቀስመው ወደፊት ለመራመድ ከተነሱ አሁን የተያዘውን ተስፋ መቁረጥና መበታተን ተወጥተው ለመጭው ትግል የሚፈለገባቸውን አስተዋጽኦ ሊያደርጉ ይችላሉ:: ማድረግም አለባቸው:: በዚህ ጥረታቸውም የመላ ኢትዮጵያ ሰሻለበት ንቅናቄ ምንጊዜም እንዳደረገው ሁሉ ዛሬም ነገም ከጎናቸው ተሰልፎ ለኢትዮጵያ ተራማጆች የትግል አንድነት፣ ለአብዮታችን ድሉና ለእናት አገራችን ክብር እየተጋፋ ወደፊት ለመራመድ ዝግጁ መሆኑን ያረጋግጥላቸዋል::

ተስፋ መቁረጥና መበታተን ይብቃ!
የኢትዮጵያ ተራማጆች ሁሉ በአንድነት ወደፊት እንገፋ!
የነቃ፣ የተደራጀ፣ የታጠቀ ሕዝብ ትግል ያሸንፋል!